# ‹‹ከርቸሌ›› በውስጥ ዓይን

(እውነተኛ የታሪክ ማስታወሻ)

ስንዱ አበበ

# «ከርቸሌ»

## በውስጥ ዓይን

## (እውነተኛ የታሪክ ማስታወሻ)

ስንዱ አበበ
1998ዓ.ም

መታሰቢያነቱ፡- ለሕፃን ዮፍታሄ ብዙዓለምአየሁ!

መብቱ የተጠበቀ ነው!

አሳታሚ፡- ስንዱ አበበ
1998ዓ.ም

የኮምፒተር ጽሑፍና የሽፋን ስዕል - ሕይወት ፀጋዬ

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በነበረው «ከርቸሌ» - የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤቶች፣ የቀድሞ ቦታው ለሌላ ጉዳይ ስለተፈለገ እየፈረሰ መሆኑን ስማሁና ለረዥም ዓመታት በዕጄ የሚጉላላው የአንዲት ጓደኛዬ የከርቸሌ ቆይታ ሰነድ ትዝ አለኝ::

ከ1991-1993ዓ.ም ማለቂያ ለሦስት ተከታታይ ግዜያቶች አንድ ዓመት ቆይታ የወጣችው ጓደኛዬ ስለከርቸሌ ማውራት ባትወድም፣ በብዙ ጉትጎታ የቻለችውን በማስታወሻ፣ የጎደለ የመሰለኝን በጥያቄና መልስ ሞልቼ ይህን መረጃ አግኝቻለሁ::

ይህ መረጃ በሴቶች እስረኞች የመኖሪያ ክልል ያለውን ሁኔታ ብቻ የሚያሳይ፣ ከከርቸሌ ብዙ ገድሎች «አባይን በጭልፋ» ታክል የተቆነጠረ እውነተኛ ታሪክ ነው::

ክፍርድ ቤት ወደ ክርቸሌ የሚያግዘን መኪና ላይ ተቆጥረን ከተጫንን እስረኞች መካከል አንድ ብቸኛ ሴት እስረኛ ነኝ::

መኪናው የፍርድ ቤቱን ግቢ ለቆ እንዲወጣ «ንዳው!» ሲል ፖሊሱ ትዕዛዝ አስተላለፈ:: እኔ እያነባሁ ነበር::

ክርቸሌ ስንደርስ ያመጣን ፖሊስ «አራንቴን» ሰጥቶ ለዋርድያው አስረከበኝ:: አምርሬ ሳለቅስ ዋርድያው «ቧ! ባክሽ አታልቅሽ! እዚህ ብዙ ጉድ ታያለሽ:: ውጭ ሀገር ሄዳለች ከተባለች፣ የደረሰችበት ጠፋ እስከተባለች ታገኛለሽ:: የምታውቂያት አታጭም:: አታልቅሽ ...» ሲል እያፅናናኝ ለመዝጋቢዎች አስረከበኝ::

አቤት! የክርቸሌ ፖሊሶች ጥያቄ አሰልቺነቱ!

ስም፣ ዕድሜ፣ አድራሻ፣ የገቡበት ወንጀል፣ ልዩ ምልክት፣ የፀጉር፣ የአፍንጫ፣ የጥርስ፣ የዓይን፣ የቁመት ... ይህ ሁሉ ተመዝግቦ ሌላ «አራንት» ተቆርጦ ወደ እስር ቤቱ እንዲያስገባኝ ዋርድያው ተጠራ:: ወደ ሴቶች ክልል «ክልል አምስት» በጠባቧ በር እንድገባ ምልክት ተሰጠኝ:: ገባሁ::

ግቢውን በርቀት ሳየው መዝናኛ ሥፍራ መሰለኝ:: እጅግ ማራኪ ነው:: ደረጃውን መውረድ ስጀምር የመላው እስረኞች ዓይኖች «በእንኳን ደህና መጣሽ!» ሊቀበሉኝ አፈጠጡብኝ!

ፖሊሱ «አላምጂት! አይዞሽ» ብሎ ተሰናበተኝ::

ሴቷ ፖሊስ ያሰለቸኝን «ምን አርገሽ ነው?» ገለመሌ አሰልቺ ጥያቄ እየጠየቀችና እየሞገተችኝ ወደ ማረፊያ ክፍል ወሰደችኝና «ፈታሽ፣ ሥነ-ሥርዓት» ብላ ጮኸች:: ለካንስ መጣራቷ ነው:: «ደልዳይ!» አለች:: መጡ::

«በኪስሽ ውስጥ ምን አለ? ገንዘብ ይዘሻል?»

የክስ ቻርጄን፣ ክብሪትና ሲጋራ አውጥቼ ሰጠሁዋት::

«ክብሪት እንዴት እዚህ ድረስ ይዘሽ ገባሽ? ክልክል ነው::» ስትል ጮኸችብኝ:: ክብሪቱን ወስዳ ሌላውን መለሰችልኝ::

«ሲጋራ ማጨስ ይቻላል?» ስል በሹክሹክታ ጠየቅኩ::

ለኮሰችልኝና እንግዳ ክፍል ትታኝ ወጣች::

በግቢው ውስጥ በከሰል ማንደጃዎች ድስቶች፣ የሻይና የቡና ጀበናዎች ተጥደው ይታዩኛል::

ፀጉሯን በቢጎዲን የተጠቀለለች ሴት ወደኔ መጣች:: ሲጋራዬን ማግ-ቡን፣ ማግ-ቡን አድርጌ ሳልረካ አጠገቤ እየተቀመጠች:-

«ምን አርገሽ ነው? ፍርደኛ ነሽ?»

ሌሎቹም ተንጋግተው ከበቡኝ::

በቢጎዲን የተጠቀለለችው ሲጋራዬን ተቀበለችኝና፣ እየተቀባበሉ ሁለት ሁለቴ ሳብ ሳብ አድርገው ተቃመሱት:: ማጌት::

ፖሊሶች «የቆጠራ ሰዓት ደርሷል፣ ደወል ደውሉ!» ሲሉ አዘዙ::

ሲጋራዬን የነጠቀችኝ ልጅ:-

«ቤት ውስጥ ማጨስ አይቻልም!» አለችኝ

ሌሎቹም፣ .«አይዞሽ! ለዛሬ በቂ ነው» በደህና እደሪ!» ብለውኝ ወደቆጠራቸው ሄዱ::

እኔም ተቆጥሬ በክፍል ቁጥር አንድ፣ በስላሳ ሰባተኛ ተራ ቁጥር ተመዝግቤ ቦታዬን ተመራሁ::

ተመርቼ ከገባሁበት ክፍል ውስጥ አንዷ በጩኸት በስሜ ስትጠራኝ በጣም ደነገጥኩ:: በአካባቢው እስካሁን እንዴት እንዳላየሁዋት እያሰላሰልኩ ሞቅ ያለ ሰላምታ ሰጠሁዋት:: እሷም ሞቅ ያለ አቀባበል አደረገችልኝ::

ትውውቃችን ከሁለት ዓመት በፊት ማዕከላዊ ማስተባበሪያ ቢሮ ታስሬ በነበር ወቅት ነው::

«እስከዛሬ እንዴት አልወጣሽም?» ስል ተገርሜ ጠየቅሁዋት

«የአስር ሺህ ብር ዋስ አጥቼ እዚሁ ቀረሁ! አለችኝ::

ጊደኞቿን መርጣ አስተዋወቀችኝ:: ሳሙና፣ የምቀይረው ልብስ ሰጥታኝ ሻወሩንም አሳየችኝ:: ተጣጥቤ ስወጣ ሻይና የምቀማምሰው ሰጡኝና ጨዋታ ተጀመረ:: ያለፈ የወንጀል ድርጊት ሊነገር:-

«እከሊት እንዲህ አርጋ ነው፣ ባሏን ገድላ፣ አሠሪዋን ደብድባ፣ በዛቻ፣ በሌብነት ... » ተዘረዘረልኝ:: የብዙዎቹ ሀጢያት ሲዘከዘክልኝ የነፍስ እናት የሆንኩ መስሎ ተሰማኝ::

ይህንን ሁሉ ስናወራ አጠገቤ ተቀምጣ የነበረች ወጣት ታራሚ አንዲትም ቃል ትንፍሽ አላለችም:: ለምን አትጫወትም? ብዬ በጥያቄ ዓይን ሳያት በሹክሹክታ «በነፍስ ግድያ፣ ባሏን ገድላ ነው የታሰረችው» ስትል ሌላዋ ነገረችኝ::

ዳግም በጥያቄ አስተያየት ስረቅ አድርጌ አየሁዋት:: የምታዋኝ አይመስልም::

ገና ወጣት ናት:: ዕድሜዋ ወደ ሃያዎቹ መገባደጃ ይገመታል:: «በምን

በደል ይሆን በዚህ ዕድሜዋ ባልዋን የገደለችው?» የሚለው ጥያቄ ከነከነኝ:: ጨዋታው ከጋራነት ወደ ግል፣ በድንገት ሲከፋፈል ይህቺው ወጣት ወደኔ ተጠግታ ስሜን በመጥራት አረጋገጠችና ራሷ ታጫውተኝ ጀመር::

«ነገሩ በጣም የተወሳሰበ ነው:: የሦስት ልጆች እናት ነኝ:: የሁለቱ ልጆቼ አባት ሞቷል:: ከሴቷ ልጄ አባት ተለያይቼ ነው አግብቼ ሁለት የወለድኩት!

የሁለቱ ልጆቼ አባት በጣም ሀብታምና ጥሩ ሰው ነበር:: ሞት ቀደመው! ሀብትና ንብረቱን ወርሼ፣ ልጆቼን ሰብስቤ ስኖር የሟቹ ባሌ እናትና ቤተሰቦች «በዚህ ዕድሜሽ ከልጅ ጋር ታስረሽ መኖር የለብሽም! የልጆቹን ድርሻና ልጆቹን ስጪንና አንቺ የራስሽን ኑሮ ኑሪ ... » አሉኝ:: ባሉኝ ተስማምቼ፣ በራሴ ድርሻ ቡና ቤት ከፍቼ መኖር ጀመርኩ::

ይህም፣ ያም «ቆንጆ፣ ቆንጆ» እያለ ሲያቃብጠኝ፣ ጥሩ ገቢ ስሠራ በመሀል ቤት ካንዱ ፍቅር ያዘኝ:: በጣም ተዋደድን:: ሥራዬን ቀይሬ አብረን እንድንኖር ተስማማንና ቡና ቤቴን ሸጬ ከሱ ጋር በትዳር መኖር ጀመርን:: ጠለቅ ያለ ፍቅር ውስጥ ነበርን::

ከጊዜ በኋላ ግን የቁም እስረኛው አደረገኝ:: በሱ ደመወዝ ብቻ የምተዳደር፣ የትም ቦታ ለመሄድ የማይፈቀድልኝ ሆንኩ:: አይርበኝም በቃ ሌላ የሚደረግልኝ ምንም ነገር የለም:: ባሌ ፀባዩ መቀያየር ሲጀምር «እንፋራረም!» አልኩት::

«ይደርሳል!» ብሎ ዘጋኝ::

በዚህ መሀል የጭብጨባ ድምፅ ተሰማና ጨዋታችን ተቋረጠ::

«አራት ሰዓት ሞልቷል! ወደየመኝታችሁ!» ተባለ:: ነገ ለመቀጠል ተስማምተን ወደየመኝታችን አመራን::

፨

ከንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት በር ተከፈተ፡፡ ደንብ ነው፡፡ ተጣጠብንና ቁርስ በየክፍላችን ጻቦ ታደለን፡፡ ጻቦ ተሰጠኝ፡፡ ሻይ ግን «ገና ኮታ አልተመደበልሽም» ተባልኩ፡፡ ሌሎቹ ከየድርሻቸው በኩባያ አካፈሉኝ፡፡

ከቁርስ በኋላ እንደመጤነቴ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀመርኩ፡፡

የሴቶች እስር ቤት «ክልል አምስት» በመባል ይታወቃል፡፡ ቁጥር አንድ የእንግዳ መቀበያ ትልቅ አዳራሽ ነው፡፡ በውስጡ ሁለት ጊዳ ተጨማሪ ክፍሎች አሉት፡፡ ከፊት ለፊቱ የፖሊሶች ማማ ይገኛል፡፡ ራቅ ብሎ ደግሞ ከሁለት ቁጥር እስከ ስድስት የተቀጣጠሉና በኮሪደር የተከፋፈሉ ክፍሎች ናቸው፡፡ ወደ መቶ ሀምሳ አራት ታራሚዎች በነዚህ ቤቶች ይስተናገዳሉ፡፡

ከቁጥር ሁለት እስከ ስድስት ላሉት ክፍሎች አራት የመፀዳጃና የመታጠቢያ ቤቶችን በጋራ ይጠቀማሉ፡፡

በከርቸሌው የእስር ክፍሎች፤ ሞት፣ የዕድሜ ልክ ፍርደኛ፣ የአዕምሮ በሽተኛ፣ ሌቦች በአንድነት በተመደቡበት ክፍል ይኖራሉ፡፡ ቁጥር አንድ እስከ ሀምሳ ሰዎችን፤ የቀሩት በየራሳቸው እስከ ሰላሳ አምስት ሰዎች ይታጎሩባቸዋል፡፡

ከፖሊሶቹ ማማ ፊት ለፊት የተንጣለለ የኳስ መጫወቻ ሜዳ አለ፡፡ ታራሚ ሲያጠፋ ወታደራዊ፣ ስፖርታዊ ቅጣትም በዚህ ሜዳ ላይ ይከናወናል፡፡ የሜዳውን ጥግ ቢሮዎችና የመሰብሰቢያ አዳራሹ ይጋሩታል፡፡ በሌላው ጎኑ የዕመጫቶች መታሰሪያ ክፍል፤ ክሊኒክና መጋዘን ሲገኝ፤ በመጋዘኑና ከቁጥር ሁለት እስከ ስድስት ባለው መሀል ቦታ በሲሚንቶ የተመረገውና ቆርቆሮ የለበሰው ጨለማ ቤት አለ፡፡

በጨለማው ቤት ከባድ ጥፋት ያጠፉ፣ ለምሳሌ ግብረሰዶም ሲፈፅሙ የተያዙ፣ የተደባደቡ፣ ... ይታሰሩበታል፡፡ መብራት'ንኳ የለውም፡፡ ጨለማ ቤት ከገቡ በቀን ሁለቴ ለሽንት ብቻ ይወጣሉ፡፡ አለበለዚያ ምግብ'ንኳ በፖሊስ አጃቢነት ነው የሚሰጥዎ!

ከረፋዱ ሁለት ሰዓት ከሰላሳ ሲሆን ፖሊሶች ይመጡና «ለሙያ ውጡ!» ብለው እስረኛውን ወደየሥራው መስክ ያሠማራሉ፡፡

እነሱ ለጥጥ ፈተላ፣ ለማዳበሪያ ሥራ፣ ለእጅ ሥራና ለልብስ ስፌት ተሠማሩ፡፡ እኔም ሲጋራዬን ለኩሼ አንዱ ጥግ ቁጭ አልኩ፡፡ የግቢው አጥር ለዓይን እይታ'ንኳ ሩቅ 'ነው፡፡ ግቢው በጣም ሰፊ!

ትላንት ገና ስገባ ፀጉሯን ተጠቅልላ መጀመሪያ የተቀበለችኝ ታራሚ

ሲጋራ ጠየቀችኝ:: ሰጠሁዋት::

«ራሴን አሞኛል ምንላርግ?»

ሲጋራዋን እየማገች - ወሬዋን ቀጠለች:: ለጤና ኮሚቴ አሳውቄ ሂጂ መታከም እንደምችል፤ አለበለዚያ ክፍል ገብቼ ጋደም እንድል መከረችኝ::

ገብቼ ጋደም አልኩ:: ይሄ መከረኛ ቡና ሱስ ነው መሰለኝ እራሴን ይፈልጠኛል:: በሸለብታ ሰመመን ውስጥ ሳለሁ ስሜ በፖሊስ ተጠርቶ ተቀሰቀስኩ:: ከቤተሰብ የመጣልኝን ስንቅና ቁሳቁስ ቆጥሬ ተረክቤ መልሼ ጋደም አልኩ::

«ተኝተሽ ህመምና ሀሳብሽን አታዳምጭ፣ ይልቅስ ተነሺና ሲጋራ እናጭስ» አለችኝ በስርቆት የገባች ታራሚ:: ተነስቼ ሲጋራዬን ለመፈለግ ስማትር

«እኔ ጋር አለ» አለችኝ::

ከቤተሰብ ስንቅና ትንሽ ፍራንክ እንደተላከልኝና ቡናም በፔርሙዝ እንዳለ ስነግራት:-

«ታዲያ! ቡናው ይጠጣ!» አለችና ቡናውን ልታመጣ ወደ ክፍል ተመለሰች:: ስኒው ቀራረበ:: ቡናው ወደጀበና ተገልብጦ ተሞቀ::

«ጓደኞቼን ልጥራቸው?» ስትል አስፈቀደችኝ::

«ጥሪያቸው!»

እጣኑን ቡል አርጋ አጨሰችው:: ሲጠሩ ወደ አምስት ደረሱ:: ሲኒዎቹ ትናንሽ ስለሆኑ ተዳረስን:: እንዳውም ለኔ ተደገመኝ:: ሲጋራ አንድ ለሁለት አንድ ለሁለት ተሰጣጡና ለኔ አንድ ሙሉ ሰጡኝ::

ሁለት ዕብድ እስረኞች በረንዳው ላይ ከተሰቀለው እስፒከር የሚወጣውን ሙዚቃ እየሰሙ ዳንስና እስክታውን አደባልቀው ያስነኩታል:: ዞር ስል በየቦታው ሁሉም ጭፈራውን አቅልጠውታል:: ያስነኩታል!

«አይዞሽ! ነገ ከነገወዲያ አንቺም ወደዚሁ ካምፕ ትቀላቀያለሽ:: ልክ እንደኛ እንደሁላችንም ትሆኛለሽ:: ገና ውሀሽ ስላልሞቀ ነው::» አለችኝ አጠገቤ እሷም እያስነካችው::

እዚህ ግቢ - ከርቸሌ፤ ማንም ማንንም አይፈራም:: ማንም ስለማንም ዓይን እይታ ደንታ እንደሌለው ገባኝ!

«እዚህ ግቢ ትላንት እንደአንቺ ደም እያለቀሰች የገባች ሁላ፣ በማግሥቱ በዜና ጭምር ለመደነስ ይቃጣታል!» አለች ሌላዋ በማላገጥ::

«ዕድሜ ለመንግሥት! ዕድሜ ለመንግሥታችን! በመንግሥታችን ዓይን ጉድፍ አይግባ! አሜን!» እየተባባሉ ተሳሳቁ።

* * *

የምሳ ሰዓት መድረሱ በደወል ተበሰረ።

የከርቸሌ ምሳ ሥነ-ሥርዓት የትም የሌለ ነው። በሰባት ሰዓት መብላት ለመጀመር በስድስት ከሰላሳ ደወል ይደወላል። ሁሉም ተራውን እየጠበቀ እጁን ታጥቦና ውሃውን በኩባያው አቅርቦ ቦታው ላይ ይቀመጣል።

መመገብ ተጀምሮ «አበቃ!» ተብሎ ደወል እስኪደወል ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ፣ መነጋገር ፈፅሞ የተከለከለ ነው።

የምግብና የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴዎች ሁኔታውን ሁሉ በንቃት የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው። ደወል ሲደወል ለእጅ መታጠብም ለሁሉም ጉዳይ መንቀሳቀስ ይፈቀዳል። ዘወትር ይህ ሥርዓት ሳይጓደል የምሳ ሥርዓቱ ይከናወናል።

የማታውን እራት ግን አራት ሰዓት ከመሙላቱ በፊት በማንኛውም ሰዓት መመገብ ይቻላል።

ከአራት ሰዓቱ ጭብጨባ በኋላ እንኳን መብላት፤ ማውራት፣ ፌስታል ማንኮሻኮሽ በፍፁም የተከለከለ ነው። ፍፁም ፀጥታ!

ከርቸሌ እንደገቡ የሚነበብልዎ ሕግና ደንብ አለ። የታራሚ መብትና ግዴታዎች:-

<u>መብት:-</u>

ማረሚያ ቤት የገባች ማንኛዋም ሴት መኝታ የማግኘት፣ በነፃ ህክምና የማግኘት፣ ማስረጃ ካቀረበች ባቀረበችው ማስረጃ መሠረት የምትፈልገውን የመማር፤ በፈቀደችውና አቅሟ በፈቀደ ሙያ መሠልጠን፣ ማረሚያ ቤቱ የሚያቀርበውን ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት የማግኘት መብት አላት።

<u>ግዴታ:-</u>

መጣላት፣ መሳደብ፣ መደባደብ፣ ከኮሚቴ ፈቃድ ውጭ ቦታ መቀየር፣ የሌሎች እስረኞች ክፍል መግባት፣ የመንግሥት ኮታ አልወስድም ማለት፣ ቁማር መጫወት፣ መስረቅ፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በገንዘብ መሸጥ ... የመሳሰሉ ነገሮች በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው።

ያጠፋ ይቀጣል። ቅጣቱ እንደ ጥፋቱ መክበድና መቅለል ይወሰናል። የሥነ ምግባር ትልቁ ቅጣት ሽንት ቤት ማፅዳት ነው። ለተፈረደብዎት ቀናት!

በከርቸሌ የጀመርኩትን ሕይወት ለመድኩት። ሳምንት፣ አስራ አምስት ቀን ... መቁጠሩን ተውኩት! ኗሪ ሆንኩ።

ከሁሉም ጋር ተዋውቀናል፣ እኔም እንደ ሌሎቹ በረንዳው ላይ መደነስ ጀመርኩ። ተላምደን! በከርቸሌ ካለነው ታራሚዎች ትልቁን ቁጥር የሚይዙት የፖለቲካ እስረኞች ሲሆኑ ሌቦች ይከተላሉ።

ቡና ራሴ አፍልቼ ጓደኞቼን መጥራት ጀምሬአለሁ። የቡና ስኒዬን፣ ጀበናዬንና ረከቦቴን እኔም አስገብቻለሁ። ጓደኞቼ «ላቦሮዎች» (ሌቦች)ና የፖለቲካ ታራሚዎች ናቸው።

ከላቦሮዎቹ መካከል አንዷ ጓደኛዬ በማረሚያ ቤቱ በተደጋጋሚ የታሰረች በመሆኗ «የማረሚያ ቤቱ የበኩር ልጅ!» ነው የምትባለው።

አዲስ አበባ ከተማ፣ መርካቶ አካባቢ ነው ተወልዳ ያደገችው። ምንም ዓይነት ትምህርት አልተማረችም። ከፍ ስትል ተባራሪ የችርቻሮ ንግድ እዛው መርካቶ ጀምራ ነበር። በዚህ መሀል በጓደኞቿ ተመልምላ ወደ «አንክቴነት» ሥራ ተሠማራች።

በከርቸሌ ግቢ ከሚፈሩ ሰዎች መካከል አንዷ ናት። እጅግ ተሳዳቢ፣ ቁጡና ተደባዳቢም በመሆኗ ሁሉም ታራሚ ይፈራታል! በጉንጯ ላይ የተጋደመው የጩቤ ጠባሳ ለአስፈሪነቷ የራሱ ሚና አለው።

ቡና ይፈላና ወሬ ይጀመራል!

ላቦሮዋ የራሷን ታሪክ እያጫወተችን ነው።

«እኔ ቤት ሰርሳሪ ሌባ ነኝ። አንክቴ ነው እምንባለው። እኛ አንክቴዎች ሥራ ስንሠማራ ለየብቻችን ነው የምንላከው። ለኛ ዓይነቱ ሥራ ረዳት አያስፈልግም። በመጀመሪያ ቤቱ ይጠናል። ሰዓቱ፣ ሁኔታው ሁሉ ይመቻችልሽና ትላኪያለሽ። ጠቃሚ የመሰለሽን ከቤቱ ውስጥ ያገኘሽውን ይዘሽ ትወጪያለሽ።

አሁን - አሁን በቅርቡኮ ነው፤ በግሩፕ መስረቅ፣ በግሩፕ መወዳጀት፣ መጠባበስ የመጣው። በኛ ዘመን ሌባ ለሌባ አይጠባበስም። አብረሽ አድረሽንኳ መነካካት የለም። የአሁን ዘመን ሌቦች እርስ በርስ እየተጠባበሱ ችግር ሲመጣም ተያይዘው ገደል!»

ከርቸሌ ጠያቂ ካላቸው እስረኞች ላቦሮዋ አንዷ ናት። እናቷና ጓደኞቿ ይጠይቋታል። እሷም የማዳበሪያ ጥልፍ እየሠራች ትሸጣለች።

«ሥራ የጀመርኩ ዘመን ገና ልጅ ነበርኩ፤ አስራ ሁለት - አስራ ሦስት ዓመቴ ቢሆን ነው። በዛ ላይ አልተማርኩም። «ዶላር» ሲባል እንጂ አይቼ'ንኳ አላውቅም። አንድ ቤት ያውም ያልተጠና አለፍ ስል ነው ያየሁት፤ ዘው ብዬ ገባሁና ሳምሶናይት አገኘሁ። ሸብ አድርጌው ወደፍሬንዶች ገሰገስኩ። ስደርስ ማንም የለም። አስቀምጬው ወደ ሌላ የተጠና ሥራ ሄድኩ»

«ከፍተሽ'ንኳ አላየሽውም?» አንዷ ጠየቀቻት

«ያኔ ምንም አላውቅም እያልኩሽ! ደግሞም ውስጡ የረባ ነገር ባይኖረው'ንኳ ሳምሶናይቱ ይፖሽራል (ይሸጣል) ብዬ ነው።

የተላኩበት ቦታ አመቺ አልሆነልኝም ነበርና ቶሎ ተመለስኩ። ፍሬንዶች ሳምሶናይቱን ከፍተው ሲፈነጥዙ ደረስኩ። በኋላ ስሰማ ሙሉውን የአሜሪካን ዶላር ነበር አሉ።

«እኔ ነኝ ያመጣሁት» ስላቸው አቅፈው ሳሙኝ። ተያይዘን ወጣን። አቤት የዛን ቀን ጭስት፤ ምግቡ፣ በርጫው፣ ሴሹ፣ ጋንጃው ቻ፤ በርቻቻ ... ሆነ።

ለኔ አንድ ሺህ ብር እንደሚበጠስልኝ ስሰማ ቂጤ ሳቀ። በማግስቱ ሺ ብሬን ሰጠኝና ጠፋ። ስንሰማ ባጭር ቀናት ደቡብ አፍሪካ ጭሯል!

ትንሽ ቆይቶ መኪና ሳይቀር ጭኖ መጣ። ሁለተኛ ይህን ሥራ እንደማይሠራ ተናገረ። በኔ ብር የሱ ሕይወት ተለወጠ።

ብር በምፈልግበት ሰዓት እንድጠይቀው ነግሮኛል። ሲደብረኝ እሄድና «ቸገረኝ፤ ሥራም እንደድሮው አይደለም። ቀዝቅዟል! ጠፍቷል!» ስለው ጥሩ ብር ይበጥስልኛል።»

አንክቴዋን ከንግሥቲቱ የተላከ መልዕክት ጨዋታዋን አቋረጣት። የከርቸሌዋ ንግሥትና አንክቴዋ ጓደኛዬ የጠበቀ ወዳጅነት አላቸው። ንግሥቲቱም አክብረውና ተሽቆጥቁጠው ይዘዋታል። ሌላው ቀርቶ ገንዘብ ከቸገራት አኩርፋ ወይም ተሳድባና አዋርዳ ትቀበላለች።

ላቦሮዋ አስፈላጊ ለመሰላት ጉዳይ፤ በተለይ ንግሥቲቱ ከሰው ተጣልተው «ስደቢልኝ፣ ገላምጭልኝ፣ አስፈራሪልኝ ...» ካሏት ወደኋላ አትልም። «ውሻ በበላበት ይጮሀል!» የከርቸሌ ትልቅ መፈክር ነው!

## የከርቸሌዋ ንግሥት፡-

በከርቸሌ ካለን ታራሚዎች ውስጥ የከርቸሌዋ ንግሥት ያላቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ከሁላችንም የላቀ ነው፡፡ እሳቸው የፈለጉትን ቢያደርጉ የሥነ-ሥርዓትም ሆነ ሌሎች ኮሚቴዎች አያገባቸውም፡፡ ኮሚቴዎች የሳቸውን ችግር እንዲፈቱ መጠየቅ የእስረኛ መብታቸው ቢሆንም፣ ንግሥቲቱን ግን ክብራቸው አይፈቅድላቸውምና አያደርጉትም፡፡

አስተዳደሩም ለእሳቸው ልዩ ዓይን ነው ያለው፡፡ በእጅም፣ በእግርም፣ በምላስም ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡

ላቦሮዋም ለሳቸው አግዛ የፈለገችውን ብትሳደብ፣ ብትማታ፣ ኮሚቴ ለአስተዳደር ቢያሳውቅም ትዕዛዙ የልዕልቲቱ መሆኑ ስለሚታወቅ ዝም ይባላል፡፡

ላቦሮዋ የተጠራችበት ደርሳ ስትመለስ ጨዋታው በሞቀ ሁኔታ ቀጠለ፡፡ ከሩቅ ብቻቸውን፣ ጀርባቸውን ሰጥተውን የተቀመጡትን፣ በሀምሳዎቹ መጀመሪያ ዕድሜ ላይ ያሉት ታራሚ ላይ እያላገጠች፣ የሳቸውን ገድል ቀጠለች፡፡

የሀምሳ ዓመቷ አሮጊት በማረሚያ ቤቱ ካሉ ሰዎች ጋር ሁሉ ፀበኛ ናቸው፡፡ ሁሉም ሰው ያጠቃቸዋል፡፡ እብዶቹ ሳይቀሩ፡፡

ወንጀላቸው፡- ከውሽማቸው ጋር «መርፌና ክር» እንደሆኑ ባል ደረሰ፡፡ ካልገደልኩ ብሎ ሲጋበዝ «በለው - በለው» ብለው ውሽማቸውን በባላቸው እጅ ማስገደላቸው ተጣርቶ፣ እሳቸው (ወ/ሮዋ) አስራ አምስት ዓመት፣ ባላቸው ዕድሜ ልክ ተፈርዶባቸው ነው የገቡት፡፡

ላቦሮዋ ማንንም ሰው አታከብርም፡፡ እሳቸውንም ሆነ ከሳቸው ዕድሜ በላይ ያሉትን ሁሉ «አንቺ» ነው 'ምትለው፡፡ «ትልቅ የአህያ ብቻ ነው!» ትላለች፡፡

«ዕድሜ ለዚች ፍንዳታ አሮጊት! ከወንዶች ጋር እንዳንተያይ'ንኳ ቀዳዳዎች ሁሉ የተደፈኑት በሷ ምክንያት ነው፡፡» በማለት ትረካዋን ቀጠለች፡፡ በዓይኗ ፈልጋ አሮጊቷን አሳየችን፡፡ ሁሉም ከት ብለው ሳቁ፡፡

«እኝህን የሚያክሉ ለምድር የከበዱ ሴት በቀዳዳ ምን አርገው ይሆን?» ብዬ አሰብኩ፡፡

አሮጊቷ ሌላ ባሏን በመጥረቢያ ከትክታ ከገደለች የዕድሜ ልክ እስረኛ ጋር ያወራሉ፡፡ በዓይን በደንብ አውቃታለሁ፡፡ አሮጊቷን ዘወትር ስትላላካቸው ትውላለች፡፡

እሳቸው ማንበብ፣ መጻፍ አይችሉም:: በሷ በተላላኪያቸው በኩል ለዓይኑካቸው ደብዳቤ ጽፈው መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ:: ምስጢረኛቸው እሷ ብቻ ስለሆነች እሷ ያለችውን «እሺ» ከማለት ውጪ አማራጭ የላቸውም::

አሮጊቷ ዓይኑካቸው በሚልክላቸው ገንዘብ እየተመሳጠሩ በቀዳዳ ከዓይኑካቸው ጋር ያወራሉ:: ይገናኛሉ:: አንዳንዴም ዓይኑካቸው በቀዳዳ ያሾልኩላቸውና ሳም፣ ሳም፤ እሽት - እሽት አድርገው ይለያያሉ::

አንድ ቀን በተለመደው ሁኔታ ላይ እንዳሉ አሮጊቷ «ብለቀው መድኃኒዓለም አይለመነኝ!» ብለው ሙጭጭ አሉ:: የቆጠራ ሰዓት ተደውሎ ታራሚው ሲቆጠር «ሰው ጎደለ!» ተባለና ተቀወጠ::

ፖሊሶች ግቢውን በዓይናቸው ቢያማትሩም ምንም የለም:: እንደገና ተቆጠርን፤ ሰው ጎደለ:: በር ተዘግቶ ፖሊስ ፍለጋ ጀመረ:: ለካንስ ወንዶችም ጋር ሰው ጎድሎ ተቀውጧል::

ፖሊሶች በወንድ ክልል በኩል ድምፅ ሰሙ:: ያውም የሲቃ ጩኸት የተቀላቀለበት:: ሰውየው በነፍስ ሲቃ ተይዘው «እባክሽ - የዛሬን! የዛሬን ...» ይማፀናሉ::

በግድ አላቀቋቸው!

አሮጊቷን ወደ ክፍላቸው፤ ሰውየው ግን ቆርቆሮው በጣም ገዝግዞ ጎድቷቸው ነበርና በአንቡላንስ ወደ ሆስፒታል ተወሰዱ::

ነግቶ፤ ጉዳዩን በዝርዝር ለማወቅ መላው እስረኛ ጓጉቷል!

ፖሊሶች ይህን ጉድ ለክልል ኃላፊዎች ለመንገር ቸኩለዋል:: «የፍስክ ወሬ፤ ተገኘ!»

ፖሊሶችን ጨምሮ መላው እስረኛ የሚስማሙበት አንድ ነገር አለ:: «ወይዘሮዋ ይህን እንደሚያደርጉ የነበረው ሃሜት፤ ዛሬ እጅ ከፍንጅ ተያዙ!» ተባለ::

እስረኞች ወይዘሮዋ የሚቀጡትን የቅጣት ዓይነት መገመት ተስኖአቸው ነበር::

«መቼም ጨለማ ቤት አይሆንም:: ምክንያቱም አሮጊቷ ከየትኛውም ቦታ ይመቻቸዋል! ይታወቃል:: ወታደራዊና ስፖርታዊ ቅጣትም አይሆንም፤ ለራሳቸው ከመቀመጫቸው'ንኳ የሚነሱት በግድ ነው:: እና ምን?» ሁሉም ጓጉቷል::

ኮሚቴዎችና የማረሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ስብሰባ አደረጉና «እኔን ያየ

ይቀጣ!» የሚል ጽሑፍ ተለጥፎባቸው በሁሉም የከርቸሌው ክልል እንዲዞሩ ተወሰነ።

አሮጊቷ ቢለምኑ፣ ቢያስለምኑ፣ እግር ላይ ቢወድቁ የማይሆን ሆነ። በቀን ሀምሳ ጊዜ የሚጠሩት ሚካኤል'ንኳ ፊቱን አዞረባቸው።

«እኔን ያየ ይቀጣ!» በትልቁ በማርከር ተጽፎ፤ ከፊትና ከኋላ ተለጥፎባቸው ሁሉንም ክልሎች ተዞሩ! ተጎበኙ።

ወደ ወንዶች ክልል ሲወሰዱ «ገድሉ 'ንጂ ማን እንደሆኑ አልታወቀም ነበርና «ዕድሜ ልክ» የተፈረደባቸው ባላቸው፤ ሚስታቸውን ሲያዩ ራሳቸውን ስተው ወደቁ። ፖሊሶች አፋፍሰው ወደ ክሊኒክ ወሰዱአቸው። ከዛን ቀን ጀምሮ የደም ግፊት በሽተኛ ሆኑ።

አሮጊቷ ሁሉንም ክልል ዞረው ሲጨርሱ ወደ ክፍላቸው ተመለሱ። ክፍሉ በፉጨትና በጭብጨባ ተናወጠ። ስማቸውን እየጠሩ በድምቀት ተቀበሉዋቸው።

ፖሊሶች ፀጥታ አስከበሩና፤ ታራሚውን ሰብስበው «... አዳምጡ! እኝህ ሰው እኔን ያየ ይቀጣ ያሉበትን ምክንያት ያስረዱናል» ሲሉ ትዕዛዝ ሰጡ።

አሮጊቷ፤ ድምፃቸው እየተርገበገበ፣ ሰውነታቸው እየተንቀጠቀጠ «ልጆቼ እናንተ'ንኳ ያላደረጋችሁትን፤ በእስተርጅናዬ እንዲህ ያለ ቅሌት ውስጥ ገባሁላችሁ። ይቅር በሉኝ» አሉና መሬት ድፍት ብለው ስቅስቅ ብለው አለቀሱ። ከዚህ ክስተት በኋላ በተለይ አሮጊቷ ማንንም ማናገር፤ ከማንም ጋር «መቁረስ» መሆን፤ ማንንም ማየት'ንኳ አቆሙ። («መቁረስ»፦ በከርቸሌ የቅርብ ጓደኛ መሆንን የሚያሳይ፤ አብሮ የሚበላ፣ አብሮ ተካፍሎ የሚኖር እንደማለት ነው።)

* * *

በከርቸሌ ከሚገርሙ ሥነ-ሥርዓቶች መርዶ አንዱ ነው።

መርዶ ሲመጣ ከፖሊሶች ጀምሮ ሁሉም ማንሾካሾክ ይጀምራሉ። ራሷ እምትረዳዋ ሴትዮ ሳትቀር አብራ ታንሾካሹካለች።

ዝግጅቱ ይቀልጣል። የከርቸሌ መርዶ የሚነገረው ከሰኞ እስከ ዓርብ ባሉት ቀናት ነው። ቅዳሜና እሁድ የጠያቂ ቀን ስለሆነ ነው። (ቅዳሜና ዕሁድ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት፤ ከሰዓት ከሰባት ሰዓት እስከ

ዘጠኝ ሰዓት ከጠያቂ ጋር ይገናኛሉ::)

ፖሊሶች የእስረኛ ቤተሰቦችን ጠንቅቀው ከማወቃቸው የተነሳ፣ ገና ከሩቅ ሰው ሲያዩ «እከሌን» ብለው ያዛሉ:: ኮሚቴ ያስተጋባል::

እስረኛና ጠያቂ በሚገናኙበት ወቅት ምንም ዓይነት ወከባ አይፈቀድም:: ለቤተሰብም ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል:: ነገር ግን ሰው ከመብዛቱ የተነሳ የሚፈጠረው ግርግርና መጨናነቅ ሲታይ የመርካቶ የዓመት በዓል ገበያ ወቅት ግርግርን ያስታውሳል::

መርዶ ለማርዳት፣ ጠዋት ገና በር ሲከፈት ሁሉም ቶሎ ተጣጥቦ ወደ አዳራሽ እንዲገባ ኮሚቴዎች ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ:: ከሰል በትልቅ ማንደጃ ተቀጣጥሎ ይገባል:: ዝግጅቱ ቀድሞ ተጠናቋል:: (ይህን መሰል ሥነ-ሥርዓት የሚፈቀደው የዓመት በዓላት ወቅት ብቻ ነው::)

በብርድ ሆነ፣ በለቅሶ መቸም ነጠላ ጣል ማድረግ ወግ ነው!

ለማርዳት የተመረጡት ብድግ ይሉና «... ያው መቸም እኛም ቢሆን ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች ነን፣ ሁሉም በጊዜው ወደ አፈር ገቢ ነውና!» በማለት የተረጂዋን ስም ጠርተው ምኗ እንደሞተ ይነገራታል::

የሚገርመው ግን፣ ሁሉም ሰው የተረዳ ነው የሚመስለው:: ወይም ለየራሱ ነው የሚያለቅሰው::

ብቻ! አነሰ ከተባለ፣ ለሁለት ሰዓታት ያህል ያለማቋረጥ ይለቀሳል:: ማንም - ማንንም አያባብልም:: ሁሉም ለሰዓታት ይንሰቀሰቃል::

ቁርስ ደርሶ፣ እዛው አዳራሽ ዳቦውም ሻዩም ይታደላል:: ለሀዘን የተዘጋጀው የመዋጮ ቀሎ ይዞራል::

የመርዶ ቀን! ሙያ መውጣት የለም:: ምሳውም አዳራሽ ይበላል:: እስከ ቆጠራ ሰዓት እየተፈራረቅን አዝነንና፣ አስተዛዝነን «እግዜር ያጥናሽ!» ተቆጥረን ይቆለፍብናል::

* * *

በከርቸሌ - ሴቶች ክልል፣ አንዲት ድመት አለች:: «ምን አወሩ» ትባላለች:: ስሟ ነው!

ሰው ሲያወራ ቁጭ ብላ ጆሮዋን አቁማ ነው የምታዳምጠው:: «ምናወሩ - ነይ» ሲሏት፣ የድምፅዎ ቅላፄ ልክ ካልመሰላት አትመጣም::

ማውራት ያቅታታል 'ንጂ የሚወራው ሁሉ የሚገባት ትመስላለች::

«ምንአወሩ? እንዲህ - እንዲህ አሉ?» ብለው አንገታቸውን ሲነቀንቁላት፣ እሷም አፀፋውን፣ አንገቷንና ጭራዋን ትነቀንቃለች::

የፖሊሱም የእስረኛውም የጋራ ጓደኛ ነች:: ሁሉም የሷ ቀላቢና ተንከባካቢ ነው!

* * *

በከርቸሌ ያለው የቡና ሥነ-ሥርዓትም ለየት ያለ ነው::

ቡና ሲፈላ የማይጠሩት የአድባርና የዛር ዓይነት የለም::

- ወሰን ጋላ - ሥራው በሠረገላ፣
- ጠቋር አባ ቡሌ
- የአሩሲዋ እመቤት አይቀሩም::

የከርቸሌው አድባር በተለይ አጠገባቸው ስላለ ነው መሰል ተደጋግሞ ይጠራል!

እንደየ ግሩፑ፣ ቡና ሲፈላ ቄጤማ፣ ፈንዲሻ፣ ቂጣ፣ ሰንደል ከብዙ በጥቂቱ የሚያቀርቡት ግብዐት ነው::

ቡናው፣ በተቀዳ ቁጥር፣ እጣኑን ቡል አርጎ ማጨስ የተለመደ ነው::

በቡና ሰዓት ብቻ የሚጠራሩ፣ ስለቡናው ክብር ብቻ ጓደኛሞች የሆኑም ይገኛሉ::

በነሱ የቡና ሥርዓት ጊዜ ለሌላ ለማንም ሰው ቡና አይሰጥም:: «ማዳችን ይበረዛል፣ ዱአችን ይበላሻል» የሚሉ በዓይነት - በዓይነቱ ይበዛሉ::

እነኝህ የቡና ማኅበርተኞች፣ ሚካኤልን! በጋራ ይወዱታል:: በተለይ ሚካኤል የሚነግስ ዕለት በግቢው የቤተክርስቲያን ቅዳሴ ከሰሙ በኋላ ያለው የቀን ውሎና፣ የቡና ሥነ-ሥርዓት እጅግ የተለየ ይሆናል::

ምርቃቱ ይኸጎደጎዳል! እየተቀባበሉ በየተራ ይመራረቃሉ::

«እነኝህን ሰዎች ይንቀላቸው፣ ደግ ዘመን ያምጣልን፣ ፍርዳችንን ያቀልልን፣ ዳኞችን ያራራልን፣ የተናገርነው ሁሉ እውነት ይሁን፣ እስረኛው ሁሉ ይፈታ፣ ይህን ቤት የእስረኛ መታጎሪያ ሳይሆን ትምህርት ቤት ያርገው፣ አይተ ይንቧችበት ...»

«መቼ?»

«አሁን!» ይላሉ በአንድ ድምፅ::

ይህን መሰሉን የቡና ሥርዓት የሚመሩት ሁለቱ አንጋፋ ታራሚዎች ናቸው:: ምግብ አብረው ባይበሉም በጣም ይዋደዳሉ:: ይተሳሰባሉ:: በዕድሜም ይቀራረባሉ::

አንዷ:- ባላቸውን ገድለው፣ መደብ እላያቸው ላይ ሠርተው ለዓመታት በማንም ሳይታወቅባቸው ኖረው፤ እንደሳቸው አባባል «መቸም፤ ልጅ ደረሰ - ቤት ፈረሰ!» ነውና የገዛ ልጃቸው መርቶና መስክሮባቸው፤ ስለተረጋገጠባቸው፤ የዕድሜ ልክ እስረኛ ሆነዋል::

ሌላዋ:- ውሽማቸውን ከሰው ጋር ተመሳጥረው አስገድለዋል በሚል ክስ ተመሥርቶባቸው፤ ለውሳኔ በቀጠሮ ፍርድ ቤት ይመላለሳሉ::

ፍርድ ቤት፤ ቀጠሮ ያላቸው ቀን በጠዋት ቡና አፍልተው፤ እርግማኑንና ምርቃቱን አዥጎድጉደው ነው የሚሸኙት:: እስኪመጡ ድረስ ጓደኛቸው ሲኒና ጀበናው ላይ አፍጥጠው ሱባኤ እንደገባ ሰው፤ እህል፣ ውሃ ሳይቀምሱ፤ እጣኑን በላይ በላይ እያቦለሉ ሲጠብቋቸው ይውላሉ:: የፍርድ ቤቱን ውሎ ለመስማት እየጓጉ::

ፍርድ ቤት ነገ ቀጠሮ ካላቸው፤ ዛሬ - ቡና ላይ ታድመው፤ የተባሉትን፣ የተኳረፉትን እያስጠሩ፤ ይቅርታ እየጠየቁ «ፍርዱ እንዲቀልልኝ - አትዘኝብኝ!» ማለትን ያዘወትራሉ::

ሁሉም ሰው «እሺ» ይላቸዋል:: ሁላችንም አንቺ ነው የምንላቸው:: አንቱ ካሉዋቸው ፀብ ይነሳል::

ለምን እንደሆነ ባልገባኝ ምክንያት ከርቸሌ ያሉ ሴቶች አንቱ መባልን አይፈልጉም::

የከርቸሌ የቡና ሥርዓትን ሌላ ለየት ባለ ሁኔታ ደግሞ የሚያከናውኑት የከርቸሌዋ ንግሥት ናቸው::

ወደ ከርቸሌዋ ንግሥት፤ የቡና ሥነ-ሥርዓት ከመታደሜ በፊት፣ ትንሽ ስለሳቸው ማውራቱ ጠቃሚ ነው::

ልዕልቲቱ፤ ካለነው እስረኞች መካከል ኩራ፣ ቀብረር ብለው ይኖራሉ:: እሳቸው ከራሳቸው ፈቃድ ውጭ አዛዥ - ናዛዥ የሌለባቸው እስረኛ በመሆናቸው ለግቢው ብቸኛ ባለመብት ሆነዋል::

«የከርቸሌዋ - ንግሥት» የሚለውን ስም ያወጡላቸው ሌቦቹ እንደሆኑ ይነገራል:: ገንዘብ «ሊፈልጧቸው» ሲሄዱ ከስሟ በፊት «እማማን» ይጨምሩበታል:: (እኔም የሁለቱንም ወገን ጥሪ አስተጋባለሁ::)

በየቀኑ ሊባል ይችላል፤ ለተወሰኑ ግሩፖች ገንዘብ ትበጥሳለች፡፡ አንዳንድ ቀን ለሌቦች፣ ሌላ ቀን ለአዛውንቶች፣ ሌላ ቀን ከፋ ብሎት ላየችው … «በጣሽ ናት!»፡፡ ዘካም ይሰጣሉ፡፡

በድንገት ተነስታ ከተጣላችዎ ግን አለቀልዎ! ጨለማ ክፍል እስከማስገባት ሥልጣን አላቸው፡፡ በሰበብ በአስባቡ አድርጋ ሁሉንም ሰው እንደየ ሙዱ ይዛዋለች፡፡ ሴት፣ የአራዳ ልጅ እንደሷ አይቼ አላውቅም!

«ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ» ለከርቸሌ ባለገንዘቦች ብዙ ርቀት ባያራምድም፤ ለኝህ ታራሚ ግን ብዙውን ርቀት አራምዷቸዋል፡፡

በከርቸሌ ግዙፍ ዓለም ውስጥ በድንገት ከተሠራ ስህተት የተረፈ እልፍ ፀፀትና ንዴት፤ በበቀልና በጥላቻ በተፈጸመ የክህደት ሰንሰለት እንደየወንጀሉ ዓይነት፤ ሰዎች ማንም ተመልካች በሌለበት እስር ቤት ውስጥ ብዙ በደሎች ይደርሱባቸዋል፡፡ በግቢው ውስጥ ያለነው ታራሚዎች በእኩል ዓይን አንታይም!

ፖሊሶች ሲያላግጡ «እኩል የምትሆኑት ፍርድ ቤት ብቻ ነው!» ይላሉ፡፡ እውነትም ነው፡፡

በቁጥር ሦስት ክፍል ልዕልቲቱ ከህያ ሁለት ደባሎቻቸው ጋር ይኖራሉ፡፡ የተለየ ቦታም ተሰጥቶዋቸው እስፕሪንግ ፍራሽና ካዝና አስገብተው (ካዝና ያላቸውና የተፈቀደላቸው እሳቸው ብቻ ናቸው፡፡) ወርቃቸው፣ ብራቸውንና መኳኳያቸውን ቆልፈው ያስቀምጣሉ፡፡ ይህን ጊዜም በምቾት ተደላድለው ለቡና ሥርዓት ይታደማሉ፡፡ ንግሥቲቱ ለብቻቸው ቆልፈው የሚጠቀሙበት የግል መታጠቢያና ማብሰያ ክፍል ተፈቅዶላቸዋል፡፡

ለየት ያለ ወሬ ሲወራ «ይህን ጉዳይ ዋና አስተዳደርዋ፣ የግቢዋ ንግሥት እንዳይሰሙ፤ ከሰሙ ያብዳሉ!» ይባላል፡፡

«እሷ እንዲህ እንደነገሰችብን ልትኖር ነው? ለሷ የዘለዓለም ቤቷ ያርግላት፤ ግቢውን እንዲህ የምታሳምረው ቤቷ ስለሆነ ነው … ለዘለዓለም ከዚህ ግቢ አትውጣ!» እያሉ የሚያማርሯት አሉ፡፡ በተለይ ከቡና ማኅበራት አባል ከአንዷ ጋር ብትጋጭ ልዕልቲቱ የዓለም ዕርግማን ሲዘንብባት ይውላል፡፡

የታራሚ ሕፃናት ልጆች ልዕልቲቱን ከስማቸው በፊት «እማማ»ን፤ ከስማቸው መጨረሻ ደግሞ «ዬ» ጨምረው አቆላምጠው ነው የሚጠሯቸው፡፡

ንግሥቲቱ ልጆችን በጣም ትወዳለች፡፡ ትንከባከባለችም፡፡ የአብዛኛውን ሕፃናት ምግብና ኮታ ትሸፍናለች፡፡ የማረሚያ ቤቱ የምግብ ኮታዋም ጠያቂ ለሌላቸው ምስኪን እስረኞች የተከፋፈለ ነው፡፡ ለወደደችው ሰው ደግ ሴት

ነች:: ለጠላቸው ግን ጭንቅ::

«ምን ታስደርገኝ ይሆን?» ብለን እንሰጋለን:: በግድ ለሷ መታዘዝና ማሸርገድ የሁሉም እስረኛ ግዴታ በመሆኑ ሲፀልዩ «ከልዕልቲቱ ዓይን ሰውረኝ» የሚሉ አሉ::

ልዕልቲቱ ቆንጆ ሴት ይወዳሉ:: አገልጋዮቻቸው ከግቢው ታራሚዎች የተመረጡት ናቸው:: ቆንጆ፣ አዲስ ታራሚ ከገባች በፍጥነት ለአገልጋይነት ትታጫለች:: ከአገልጋይ አገልጋይ የየራሱ የሥራ ድርሻ አለው:: ከወሬ ማቀበል፣ መታመንና እስከ ቤት ዕዳት ሥራ የተመደቡ አገልጋዮች በየአስራ አምስት ቀኑ፤ ከሥራ ሥራ ይቀያየራሉ:: የሚሾሙ፣ የሚሻሩም ሞልተዋል:: ላገለገሉበት ከጥሬ ገንዘብ እስከ ሶፍት፣ ሳሙናና ምግብ እንደየቅርበታቸው ይሰጣል::

ዋናዋ ተመርጣ የምትመደበው ልዕልቲቱን ማሸት (ማሳጅ ለማድረግ) ነው:: በርሳቸው ክፍል የተመደቡት ሁሉ ንፅህናቸው በንግሥቲቱ ቁጥጥርና ክትትል ስር ነው::

ንፅህናዋን የማትጠብቅ፣ ንግሥቲቱ ከመተኛታቸው በፊት ያሸለባት፤ ያንቀላፋች፤ እሳቸው ከመንቃታቸው በፊት ነቅታ የምታወራ፣ የምታሾካሹክ ... ብቻ በሰበብ በአስባቡ ጉዷ ይፈላል::

በርሳቸው ክፍል ያለች ታራሚ ታማ እንኳን ቢሆን ንግሥቲቱ እንደነቃች መነሳት ግዴታዋ ነው:: ደፍራ በፀጥታ ተኝታ ካረፈደች ቀስቃሽ ሰው ይላክባታል:: ከማለዳው ቆጠራ በኋላ መተኛት አይፈቀድላቸውም:: «ቤቱ ሊፀዳ ነው ብላችሁ አስነሱዋቸው» የሚል ቀጭን የልዕልቲቱ ትዕዛዝ ይፈፀማል::

ልዕልቲቱ ዘወትር ከዕንቅልፋቸው ተነስተው፣ በደንቡ መሠረት አንደኛ ተቆጥረው መታጠቢያ ቤት ይገባሉ:: ረዥም ሰዓት መታጠቢያ ቤት ያሳልፋሉ::

በዚህ ሰዓት አገልጋዮች ከአራት ዓይነት ያላነሰ ቁርስና ጭማቂ አዘጋጅተው ይቆያሉ:: ንግሥቲቱ ቁርሳቸውን በእርጋታ ተመግበው፤ ልክ ቢሮ እንደምትሄድ ሴት ተኳኩለውና ተጋጊጠው እስኪጨርሱ ግቢው በተለመደ የራሳቸው ቦታ ላይ ቡና መቀራረብ ይጀምራል::

የርሳቸው ቡና ሲቀራርብ ለዕለቱ የተመረጡት አጣጭና አጨዋቾች ቦታቸውን ይይዛሉ:: አንዳንዴም ለነገ ቡና ዛሬ የአክብሮት ጥሪ የሚደርሳት ሴት በዕለቱ ዘንጣ እንድትመጣ ትዕዛዝ ይደርሳታል:: በመጨረሻ ንግሥቲቱ ይመጡና በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ይታደማሉ::

በማጨሻው ላይ እሳት ተደርጎ ከዕጣን ጋር ይቀርብላትና በማንም ሳትሰማ ፀሎቷን አሳርጋ እጣኑን ቡል አርጋ ታጨሳለች። የቡና ቁርሱም በመጀመሪያ ለሷ ይቀርብላትና ቀምሳ በመለጠቅ ለዕድምተኛው ይዞራል።

በሷ የቡና ሥነ-ሥርዓት የታደመ ማንም ሰው ቡናው ሳያከትም መንቀሳቀስ አይችልም። አፍሊዋን «በአደብ ሆነሽ አፍይው!» ትባላለች። ይህን ሥርዓት ያጓደለም ከባድ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ሁለተኛ ቡናዋ ላይ እንዳትደርስ ይደረጋል።

ቡናው ሲጠናቀቅ ንግሥቲቱ ወደ አስተዳደር ቢሮ ትሄዳለች። ስታወራ፣ እስረኛ ስትወነጅል፣ ስትጫወት ትቆይና ለምሳ ሲደወል ትመጣለች። ምሳው ግዴታ ስለሆነ ሕግና ደንብ አክብራ በልታ ተመልሳ ወደ ቢሮ ትሄዳለች።

ንግሥቲቱ - ከንግሥትነታቸው በተጨማሪ ጥይት ነጋዴ፣ ባለሀብት ናቸው። ከርቸሌ ግቢ ውስጥ ለሱቅ የሚሆን አንድ ክፍል ተሰጥቷቸዋል። (ይህን ዕድል ያገኙም ብቸኛዋ ሴት እሳቸው ብቻ ናቸው።)

ዘይት፣ ከሰል፣ ቡና፣ ዕጣን፣ ጨው ... የመሳሰሉ ሸቀጣሸቀጦችን ከውጭ የራሳቸው ሰዎች እያቀበሉዋቸው ለኛ ለግቢው እስረኞች ይቸረችሩልናል።

ለዚሁም ሥራ ሁለት ሠራተኞች ተቀጥረዋል። ሱቁ ከሰኞ እስከ ዓርብ ክፍት ሲሆን ቅዳሜና እሁድ የጥየቃ ቀን ስለሆነ፣ ዓርብ ዓርብ የምንፈልገውን ቅድሚያ እንድንሸምት ይነገረናል።

በከርቸሌ ቆይታዬ ንግሥቲቱ ክፍል ተመድባ በአልታዘዝም ባይነት ወደኛ ክፍል የተዛወረችውን የሀያ አንድ ዓመት ታራሚን የማልረሳት፣ ከልዕልቲቱ ተጋጭታ ምንም ጉዳት ያልደረሰባት ብቸኛ ሰው በመሆኗ ጭምር ነው።

«በአልሞት ባይ ተጋዳይ» ፋይል ክስ ተመሥርቶባት ገና በቀጠሮ ፍርድ ቤት ትመላለሳለች። ከኔ ጋር መቁርሶች ሁነናል። ሁሉም ሰው በግልፅነቷ ይወዳታል። በደረሰባት ክፉ እጣ ያዝኑላታል። ንግሥቲቱም ሊገስጿት ያልቻሉት በዚሁ ምክንያት ነው። ወይም ሳይሆን አይቀርም።

የዚህችን ታራሚ ዝርዝር ችግር አብዛኞቻችን በግል ለምክር እየተጠየቅን (እየጠየቀችን) አውቀነዋል። «ሙሽራዋ!» ሲሉ የሚያቆላምጧትም አሉ። በከፍተኛ ደረጃ ጠያቂ ያላት ታራሚም ነች። ስለባልዋ ሁሉንም ሰው ታማክራለች።

«ከተጋባን ዓመት'ንኳ አልሞላንም ነበር፤ በቃ ምን ብዬ ልንገርሽ እጅግ በጣም ነው የምወደው፤ ባሌን ሳስብ መላሰውነቴን ሁላ ውርር ያደርገኛል:: አንቺ ባልሽን ስታስቢ እንዲህ ይሰማሻል? እኔ ግን ምንላድርግ?» የዘወትር ጥያቄዋ ነው:: ስለባልዋ ስታወራ ሁሌ ታለቅሳለች::

«ከሱ ሌላ ምንም ወንድ አላቅም!» ትላለች:: ቤተሰቦቿ ባይፈቅዱም እነሱ ስለተዋደዱ እምቢ ብለው ተደግሶ ተዳሩ:: ለካንስ ሌላ የሚወዳትና የሚፈልጋት የሰፈር ጎረምሳ አለ:: በማግባቷ ተበሳጭቶ መረበሽ ጀመረ:: ከባልዋ አልፎ ቤተሰቦቿ ጭምር ጉዳዩን አውቀዋል:: ጎረምሳውም አልተቻለም::

አንድ ቀን ከባልዋ ጋር አመሻሽተው ወደ ቤታቸው ሲገቡ መንገድ ጠብቆ ፀብ ገጠሙ:: ጎረምሳው የታጠቀውን ጩቤ ሲመዝ ባል አስጣለና ነጥቆ ደጋግሞ ወጋው:: እሷም በድንጋጤ ከባልዋ እጅ ጩቤውን ነጥቃ «ተንደርድሬ ሰው ቤት ገብቼ ጩቤውን ሽንት ቤት ከተትኩት» ትላለች:: በዕለቱ ከሆነው የምታስታውሰው ይህን አጋጣሚ ብቻ ነው:: እሷም፣ ባሏም ከርቸሌ ናቸው::

ይህች መልከ መልካም ወጣት በየዕለቱ የምትናፍቀው አጋጣሚ አላት:: የጠበቃዋን መምጣት:: ጠበቃዋ ሲመጣ ቢሮ ትጠራና ከባልዋ ጋር ዓይን ለዓይን ይተያያሉ:: ጠበቃዋ መጥቶ ባሏን አይታ ከመጣች በኋላ እንደ አዲስ ማልቀስ፣ ማስታወስ፣ መረበሽ ትጀምራለች::

* * *

በከርቸሌ የሴቶች የእስር ክልል ከፍተኛውን ቁጥር የሚሸፍኑት አብዛኛዎቹ ገጠር ቀመስ ከተሜ የፖለቲካ እስረኞች ናቸው:: በዕድሜ ሕፃናት የሆኑ (ከአስራ አምስት ዓመት በታች አሉ::)

እነኝህን መሰሎቹ ፍርድ ቤቱ ለዕድሜ ምርመራ እንደላካቸው ይናገራሉ:: ከዛ በኋላ ፍርድ ቤት ቀርበው አያውቁም:: ከሦስት ዓመታት በላይ የቆዩ ይገኙበታል::

እነኝህ የፖለቲካ እስረኞች ፊታቸው ላይ የጀግንነት፣ የቆራጥነት፣ የጉብዝና ስሜት ይነበባል:: ብሔራቸውን የአምልኮት ያህል ያፈቅራሉ:: ሌት ተቀን ስለብሔራቸው፣ ስለትግል ታሪካቸው ማውራትን መስበክ ይወዳሉ:: በዚሁም መኩራራት ያበዛሉ:: ለየዘራቸው፣ ለየአካባቢያቸው ያደላሉ::

ከመሀላቸው ማናቸውም «ወንጀለኞች» ነን ብለው አያስቡም:: አያምኑም:: አልፎ አልፎ በወሬያቸው መሀል ግን ጨካኝ ገለፃዎቻቸው ያስደነግጣሉ:: ከገለፃቸው ምን ያህል ጨካኝ እንደሆኑ ለመገመት ይቻላል::

እንኳን ከሌላ የርስ በርስ ፀባቸው ያስፈራል:: ከነሱ ጋር ፀብ በፍፁም አያስፈልግም:: በሚያደርጉት ድርጊት ሁሉ መኩራራትና መመፃደቅን ያበዛሉ:: ሁሉም እስረኛ ከነሱ ፀብ ተጠንቅቆ ነው:: ኩርፊያቸው ለትዕግሥትም፣ ለመግባባትም አያመችም:: በሁሉም ጉዳይ ቶሎ ለፀብ ይጋበዛሉ::

እርስ በርስ ሲጣሉና ሲሰዳደቡ ቃላት'ንኳን አይመርጡም:: ከንግግር በላይ እጅና እግራቸውን እየተጠቀሙ የሚሰዳደቡትን ማየት ያስፈራል:: ለነሱ ግን ደንታቸውም አይደለ::

ሁሉም ስለተከሰሱበት ወንጀል ሲያወሩ በጣም እያቃለሉ ነው:: አንዷ «ቤት አከራዬሽ ተብዬ»፣ ሲስተሯ ደግሞ «ወንጀለኛ አክመሻል ተብዬ» ዓይነት:: ሲጣሉ ግን፤ በፀብ ስድድብ ሰዓት «የሰው ደም ከላሰ ሰው ጋር ንግግር ጨረስኩ!» ይባባላሉ::

አብዛኛዎቹ ከዝዋይ ወደ ከርቸሌው እስር ቤት የሚመጡት፤ ለህክምና ወይም ለፍርድ ቤት ቀጠሮ ነው:: «ጉዳያችን በክልላችን ባለ ፍርድ ቤት ይታይልን ብንል የሚሰማን አጣን» ሲሉም ይማረራሉ::

ከዝዋይ ሲመጡ ለሚወዱት ሰው ከሰል፣ የገንፎ እህል፣ ቅንጨ በማምጣት ያከፋፍላሉ:: ካልመጡም የሚላክ ሰው ካገኙ ይልካሉ:: ደብዳቤብ ይፅፉልናል:: እኛም በአፀፋው ምላሽ እንሰጣለን::

እስረኛ ለእስረኛ በአብዛኛው የምግብና የህመም ጉዳዮች ላይ ይተሳሰባል::

* * *

በከርቸሌ ያሉ የአዕምሮ በሽተኞች ዓይነት፣ ብዛት ደግሞ ሌላው የግቢውን ገፅታ የሚያሳይ ትልቅ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን:: የእብደታቸው ዓይነትና ሥርዓት ደግሞ የተለያየ ነው::

በመድሀኒት የሚታዘዙ፣ መድሀኒታቸው አልቆ የፈዘዙና የደነዘዙ፣ ገና ሆስፒታል ለመሄድ በቀጠሮ የሚጠባበቁ፣ ተኝተው የሚውሉ፣ የሚጨፍሩ፣ ፀብ-ፀብ የሚላቸው ... ዓይነቱ ብዙ ነው::

ጊደኞች የነበሩትን ሁለቱን እብዶች ግን አልረሳቸውም::

ሁለቱም ከኔ በኋላ በአስራ አምስት ቀን ልዩነት ተከታትለው ነው ከርቸሌ የገቡት::

አንዷ የምታወራው፤ መያዣ መጨበጫ የሌለው ወሬ ነው:: ብቻ «ባሌ ልጄን ቀምቶኝ ነው ለዚህ የበቃሁት» ትላለች::

«እሰው ግቢ ተኝቼ ተገኝቼ ሌባ ብለው እዚህ አጋዙኝ» የምትለው ታማሚ፣ ታራሚ፤ ሰው ቤት ተቀጥራ ስትሠራ፤ የሴትየዋ ባል ደፍሯት እንዳረገዘችና ስታረግዝም ከቤታቸው እንዳባረሯት ትናገራለች::

ተቸግራ ወልዳ ሄዳ የልጇ አባት እንዲረዳት ስትጠይቀው ልጁን ነጥቆ ለዚህ እንዳበቃት እርግጠኛ ሆና ቀኑን ሙሉ በረዥሙ እየጮኸች ስታወራ ትውልና ሲደክማት አንድ ጥግ ኩርምት ብላ በማይሰማ ሁኔታ ከራሷ ጋር ማውራቷን፣ መሳቋን፣ ማልቀሷን ትቀጥላለች::

ቡና ሲፈላ ያየችበት ሄዳ ቁጭ ትላለች:: አትጠይቅም:: ከሰጡዋት ግን ትጠጣለች:: ከሰው ጋር ጨርሶ አትነጋገርም:: ሁሌ ብቻዋን እንዳወራች ነው::

አማኑኤል ሆስፒታል ልትወሰድ ወረፋ እየጠበቀች ነው:: በጣም ስለምታሳዝን ብዙው ሰው ይራራላታል:: ስትመጣ ጫማ'ንኳ አልተጫማችም:: የግቢዋ ንግሥት ለጤና ኮሚቴ ተናግረው ልብሷን እንድትቀይር፣ ገላዋንና ፀጉሯንም እንድትተጣጠብ አስደረጉ:: ቅባት፣ ጫማና ልብስ እሳቸው ሰጡዋት:: ቡናም ስትፈልግ እሳቸው ጋር እንድትጠጣ ነገሯት::

ተራዋ ደርሶ አማኑኤል ሆስፒታል ልትወሰድ እንድትዘጋጅ ተደረገና ተወሰደች:: መድኀኒት ታዞላት መጣች፤ ጧትና ማታ - አንድ አንድ ፍሬ የሚዋጥ::

ከአማኑኤል ስትመለስ መኪና ውስጥ ተኝታ መጣች:: እንደመጣች በግድ ተቀስቅሳ ምሳ እንኳ ሳትበላ ተኛች:: እራት በመከራ ተቀስቅሳ በላች:: ተኛች:: መተኛት - መተኛት::

ጭራሽ ለመፀዳዳት'ንኳ መነሳት አቃታት:: ሽንቷን በተኛችበት መልቀቅ ሆነ:: የሷን ፍራሽና ብርድ ልብስ በየቀኑ መቀየር የሰለቻቸው የጤና ኮሚቴዎች ለበላይ አካል አሳወቁና ቦታ እንድትቀይር፤ እዛው ክፍል የሽንት ቤቱ መግቢያ አጠገብ እንድትሆን ተደረገ:: ግን ሰላማዊ ዕብድ ነበረች:: ነች::

ሌላዋ ደግሞ «ቡና ቤት ደህና ስሠራ ተቀናቃኝ መድሀኒት አበላችኝ:: መድሀኒት አደረገችብኝ» ነው የምትለው::

የታክሲ መስታወት ሰብራ ነው ከርቸሌ የገባችው:: «አሁንም አልለቃት - አነካክተዋለሁ!» ትላለች ደጋግማ::

መሳደብ፣ መለፍለፍ፣ የሰው እቃ መንካት፣ ሰው መተናኮል ሥራዋ ነው! እንኳን ታራሚ ፖሊስ ቢቆጣት ደንታ አይሰጣትም:: የግቢውን መላ ታራሚ ትቀውጠዋለች::

ከመሬት ተነስታ ማንን እንደሆነ'ንኳ በማያስታውቅ ሁኔታ መሳደብ፣ ክፍሉን መረባበሽ፣ የቡና ስኒዎቻችንንና መጠጫ መመገቢያ እቃውን ሁሉ ትሰባብራለች:: እሷ ከመጣች ጀምሮ ድስት፣ ሻይ፣ ቡና ጣድ አርጎ ዞር ማለት ቀረ:: ድስቱን ከፍታ ወጥ እያማሰለች መላስ፣ ወይም እንጀራ ፈልጋ ገልብጣ መብላት ቢመቿት፣ ቢሰድቧት ደንታ የማይሰጣት ናት:: ዱላ አንስታ ለመማታት ሁሉ ይቃጣታል:: ለደቂቃ'ንኳ የማትተኛበት ቀናቶች ይበዛሉ:: ለሷም ቀጠሮ ተይዞላታል:: ግን አልደርስ አለ::

ከአቅም በላይ ሆነች:: አንዱ ክፍል ገብታ ያገኘችውን ሰው ልብስና ጫማ ትገደግድና ፋሽን ሾው ታሳያለች:: የዕቃው ባለቤት ሲቆጣት ደንገጥ'ንኳን አትልም:: ጭራሽ ይባስ ብላ የስድብ መዐት ታወርዳለች:: ፖሊስ ካልተጠራም አታወልቅም::

ስታስመርረን ልብስና ጫማችንን ተንተርሰን መተኛት ግድ ሆነ:: ሲቸግረን «ኡ!ኡ!» ብለን እጇን በካቴና አሳሰርናት:: በምግብ ሰዓት ብቻ ትፈታለች:: እጇ ቢታሰርም የየሰውን ጫማ መቀያየር ጀመረች:: እግሯም ጭምር በካቴና ታሠረ::

እጇም እግሯም ታስሮ እሷ ግን እንጣጥ - እንጣጥ እያለች በቀሚ ሰው ላይ እየወደቀች መበጥበጥዋን ቀጠለች:: እራት ለመብላት ችግር ሆነ:: በተለይ ብቸኛዋ አዛውንት ታራሚ ሊበሉ ሲያቀራርቡማ ይብስባታል!

እሳቸውም ጀርባቸውን ሰጥተው ነው የሚበሉት::

«ዋ ሙ! ጀርባሽን ሰጥተሽ ብቻሽን ዋጭ፣ መቸም እንብላ እናትሽን ገድሎብሻል! አንቺ ሆዳም ...» እያለች ትወርድባቸዋለች:: እሳቸው ላይ የምትብሰው ምንም ስለማያቀምሷት ነው::

እየደጋገመች፣ እየጨማመረች ስትጮህባቸው:-

«ኮሚቴዎች ልብ አርጉልኝ፣ ኋላ በኔ እንዳይሳበብ፣ ከስሼ እንደታሰረች ጨለማ ቤት ነው የማስገባት» እያሉ ይፎክራሉ:: እሳቸው አዘውትረው «ጨለማ - ቤት ጨለማ ቤት» ማለት ያበዛሉ::

እሳቸው ጨለማ - ቤት መግባት በጣም ይፈልጋሉ ተብለው ይታማሉ:: ምን አድርገው እንደሆነ 'ንጃ (እኔ ከመታሰሬ በፊት) ለአንድ ወር ጨለማ ቤት ተፈርዶባቸው፣ ገብተው እንደነበር፣ ከጨለማ ቤት ሲወጡ እጅግ አምሮባቸው እንደወጡ የሚያስታውሱ አጫውተውኛል:: (ለካንስ «እኔን ያየ ይቀጣ!» የተፈረደባቸው፣ ጨለማ - ቤት ቢያስገቡዋቸው ደስታቸው መሆኑ ስለሚታወቅ እንደሆነም ሰምቻለሁ::)

ብቻ አሮጊቷ ያብዳሉ:: አንዳንድ ቀን እሳቸው ከሷ በላይ ያበዱ ይመስላል:: ማንም፣ ምንም አይልም:: ምክንያቱም ምንም የሚመጣ ነገር ስለሌለ:: አሮጊቷ በሷ ምክንያት አፍ አውጥተው «ኧረ ተው - ሚካኤል ተው - ተው፣ እዛው ጨለማ ቤቴ ይሻለኛል፣ አልኩህ እኮ!» ብለው አምላካቸውን እስከማማረር ይደርሳሉ::

«ዋጮ! ዋጭ! ዋጮ! ...» ለሰዓታት እየጮኸች፣ እሳቸውን እያየች ትሳደባለች::

ሲብስባቸው እሳቸው «ኡኡ» ብለው ይጮሀሉ:: ፖሊሶች ምን እንደተፈጠረ ለመጠየቅ በተደጋጋሚ ካልጮሀን በስተቀር ብቅ'ንኳ አይሉም:: ብቻ እሷ ፊት ምግብ መብላት ከፍተኛ የስድብ ናዳ የሚያከናንብ ሀጢያት ነው::

ሀያ ስምንታችንም ተስማምተን አንድ ነገር እንዲደረግ በኮሚቴ ተስማምተን ለአስተዳደር ዝርዝር ሁኔታውን እንዲያውቁ አደረግን:: ኮሚቴ - ለአስተዳደር፣ አስተዳደሩ ዝም አለ::

ፖሊሶችን ቀን-ቀን እንደልቧ ስትሳደብ፣ ሀገር ላይ እርግማን ስታወርድ ዓይናቸው ያያል፣ ጆሮዋቸው ይሰማል::

«ቀጠሮዋ አልደረሰም!» በሚል ዝም ብለዋል:: ከአምስት ወራት:: ጥበቃ በኋላ ተራዋ ደርሶ አማኑኤል ሆስፒታል ተወሰደች:: መድሀኒቱም አላበረዳት:: ያው እጇንም እግሯንም እንደታሰረች ... ከርቸሌ::

በከርቸሌ ወዳሉ ቡድኖች ስንመጣ ደግሞ፣ ተመራርጠው ጊዜያቸውን አብረው የሚያሳልፉ ጓደኛሞችን እናገኛለን:: ከንግሥቲቱ ቀጥሎ ሠራተኛም ያላቸው፣ በቂ ጠያቂና ገንዘብም ያላቸውና ከየወንጀሉ ዓይነት ተመራርጠው በጋራ የተጎዳኙ ናቸው::

ከነኝህ ታራሚዎች መካከል «በከባድ ስርቆት» ተከስሳ ገና ፍርድ ቤት የምትመላለሰው ወጣትና «በማጭበርበር» አራት ዓመት የተፈረደባት ታራሚ

ከሌሎች ሦስት ታራሚዎች ጋር በመሆን የጋራ ግዜን በማሳለፍ ይታወቃሉ::

ትንሽ ቆይቶ ሁለቱ ወጣቶች ሴትነታቸውን ረስተው እንደ ባልና ሚስት መሆን ጀመሩ:: ከቆጠራ በኋላ አንዳቸው ፍራሽ ላይ አንድ ጋቢ ለሁለት እየለበሱ ይተሻሻሉ:: ሰው ሁሉ ተኝቶ፣ ቴሌቪዥን ጠፍቶ እነሱ አይላቀቁም:: ይህን ሁኔታ ብዙ ጊዜ በምክር፣ በቅጣት ቢታለፉም አሻፈረን ብለው ቀጥለውበታል::

አንድ ቀን ኮሚቴዎችና የክልል ሀላፊዎች ተነጋግረው ቤት መቀያየርን እንደ አማራጭ አድርገው አንዷን ወደ ሌላ ክፍል ቀየሯት:: ወጣቷ ጊደኛዋ ይህን ውሳኔ ስትሰማ ራሷን ስታ ሲሚንቶው ላይ ተፈጠፈጠች:: (ሚስት ስለሆነች ነው እንዲህ የሆነችው ይላሉ::) ራሷን አውቃ ስትነቃ፣ በለቅሶና በሀዘን ምግብ መብላት'ንኳ አቃታት:: ታማሚ ሆነች::

ቀን - ቀን ግቢው ውስጥ ጥግ መርጠው መቀመጥ ሲጀምሩም ተከለከሉ:: ትንሽ ቆይተው አረሳሱና አብረው መዋል ጀመሩ:: እነሱን ላለማየትና ለማለያየት ብዙ ቢሞከርም አልተቻለም:: ጭራሽ አንዷ «ተው'ንጂ፣ አብረን መብላት እንኳ ይፈቀድልን» ብላ አስፈቀደች:: እስከ አራት ሰዓት ምሽቱን አብረው መሆን ተፈቀደላቸው:: ፍቅራቸው ያስቀናል:: በጣም ይተሳሰባሉ:: በተለይ ታናሽየዋ ታሳዝናለች:: ብዙ ጠያቂ ስላላት ወዳጅዋ በምንም ነገር አትቸገርም::

* * *

ከርቸሌ አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸው ከአስራ ሦስት - አስራ ሰባት ዓመት የሚገመቱ በርካታ ታራሚዎች አሉ:: «ተመላሉ» ይባላሉ::

«ተመላሉ»፣ ተመላላሽ እስረኞች ማለት ሲሆን፣ ከነኝህ ውስጥ በርካታዎቹ የጎዳና ተዳዳሪዎች ናቸው:: ፍርድ ቤት ዕድሜያቸውን ከግምት እያስገባነው መሰል ትልቁ ፍርዳቸው ከዓመት አይበልጥም:: ይፈታሉ:: ግን በዓመቱ በተለይ ክረምት ሲመጣ ተመልሰው ይመጣሉ::

እነሱም ይህን ጠንቅቀው ያውቃሉ ወንጀል መሥራቱንም ሥራዬ ብለው እንደተያያዙት ይናገራሉ::

«የክረምቱን ብርድና ችግር ማን ይችለዋል፣ እዚህ ገብቶ በመንግሥት መቀለብ ነው'ንጂ:: ለኛ ብሎ አይደለም የሚቀልበን፣ ግዴታው ነው:: የዜግነት

ድርሻችን ነው!» ይላሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ማረሚያ ቤት ከሚገኙት አራት ታራሚዎች መካከል አንዷ ወንዳወንድ ነች። አለባበሷም፣ የፀጉር እስታይሏም።

ይህች ልጅ የከርቸሌ ልዩ ስሟ «አዬ በጉልበቱ» ነው። ነገር ግን እንደጎዳና ተዳዳሪነቷ አይደለችም። ገንዘብ ከከፈሏት ልብስ ጭምር ታጥባለች። ከምንም ነገር በላይ የሲጋራ ሱስ አትችልም። ለሲጋራ ገንዘብ ጠይቃ (ገንዘብ ያለውን በምን እንደምታውቅ እንጃ) ከከለከሏት አለቀ። ጥምድ አድርጋ ትይዛለች። በተለይ አሮጊቶቹ ላይ ትብሳለች። ቡና አፍልተው እርግማን፣ ከምርቃት ደባልቀው የሚሉትን፤ በደህና ቀን የሰማችውን ገለባብጣ መራገም ትጀምራለች።

የአድባሩን፣ የአውጋሩን ስም ሁላ ትጠራና «እነኝህ ኑሮ መሯቸው ትልቅ ወንጀል እየሠሩ የሚገቡትን፤ የኛን የተመላሉዎችን ቦታ የሚያጣብቡትን ሁሉ ቅዱስ ሚካኤል የዘላለም ቤታቸው ያድርግላቸው። ጠያቂዎቻቸው ይሰልቹዋቸው፤ ዞር ብሎ የሚያያቸው ይጥፋ፤ ወጣት - ወጣቱ ብቻ ይውጣ! እኛ ተመላሉዎች ወጣ ብለን ጉዳያችንን ፈፅመን እንምጣ!» ትላለች።

እጣኑን ቡል አርጋ እያጨሰች «እኛ ስንወጣ ቅናት፤ ተመልሰን ስንመጣ ቅናት፤ ወንዶች አይደለን ምን እናርጋችሁ?»

ከንግሥቲቱ ከተጋጨች «አንቺም ሌባ፣ እኔም ሌባ። እንደውም አንቺ ሞልቶ - ተርፎሽ የምትሰርቂ እኔ ግን ተርቤ ...» አፏ ሰው ያዋርዳል። ካልደረሱባት ግን ማንም ላይ አትደርስም። ሳንቲም ስሙኒ ካገኘች ይበቃታል! ለሲጋራዋ!

ጓደኞችዋ በርስዋ እርዳታ ነው የሚኖሩት። በጣም ይተሳሰባሉ። ምንም ጠያቂ የላቸውም።

ከነኝህ ታራሚዎች መካከል በጣም ትንሿ በጣም ዓይነአፋርና ዝምተኛ ነች። «አዬዋ» ሲፈቱ በጋራ የሚሠሩትን ታስለጥናታለች። ሌላዋ «ሚጣዬ!» ነች።

ሚጣን ሁሉም ሰው ይወዳታል። ከታራሚ እስከ ፖሊስ ፀጉር ስትሾርብ ትውላለች። ፖሊሶች ጠቀም ያለ ፍራንክ ይሰጡዋታል። በየክልሉ ብዙ ዓይነካዎች አሉዋት። ኪነትም ነች።

ለአንድ ዓመት በዓል ከክልላችን ወደ ሌላ ክልል ተወስደን ኪነት በማየት ላይ እንዳለን መሸለም ተፈቀደ።

ሚጣን የማይሸልማት፣ የማይስማት ወንድ አልነበረም፡፡ ከኪነቶች ሁሉ እሷ ብዙ የገንዘብ፣ የከረሜላና የማስቲካ ስጦታ ጎረፈላት፡፡ ተንበሽብሻ መጣች፡፡

በማረሚያ ቤቱ ብዙ የዓመት በዓላቶችን አሳልፌያለሁ፡፡ በተለይ የዘመን መለወጫ በዓል ሲሆን እጅግ ይደምቃል፡፡

የዘመን መለወጫ በዓል ሊደርስ ሲቃረብ፣ የማረሚያ ቤቱ የኪነት ቡድን ልምምዱን ይጀምራል፡፡ ዘፈን፣ ድራማ፣ ጭውውት፣ ቀልዶ-ቀልዶች ይዘጋጃሉ፡፡ የኪነት ቁሳቁሶችንና አልባሳቱን የሚያቀርበው ማረሚያ ቤቱ ነው፡፡

በነሐሴ ወር መገባደጃ የ«አሸንዳ» በዓልን የትግራይ ተወላጅ ታራሚዎች እጅግ ተውበውና ደምቀው፣ ቤት - ለቤት እየገቡ (እንደ አበባ ሆዬ ሆይ ነው) ይጨፍራሉ፡፡ ፖሊሶች ጭምር ገንዘብ ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ ጀምሮ የበዓል ዝግጅቱ ይጧጧፋል፡፡

እኛም እንደየሙዳችን ተመራርጠን የበዓል ዝግጅቱን እናጧጡፋለን፡፡ ለበዓሉ ቀን የሚጠጣ ነገር ለማዘጋጀት፣ አፖፕ፣ የተገኙ መድሀኒቶች በሙሉ ተጨምረውበት ይበጠበጣል፡፡ ለዚህ ሥራ ማንኛውም መድሀኒት ተስማሚ ነው፡፡

የአዕምሮ በሽተኞች ኪኒን፣ አምፒሲሊን፣ ቴትራሳይክሊን፣ ማስታገሻዎች አይጠፉም፡፡ እንዲያፈላው ኮካ ወይንም ፔፕሲ ይጨመርበታል፡፡ ጠንከር ያለ መጠጥ ይወጣዋል፡፡

በበዓሉ ዕለት ማረሚያ ቤቱ ከወትሮው ለየት ያለ፣ ሥጋ ጣል-ጣል የተደረገበት ምሳ ያቀርብልናል፡፡ ከቤተሰብ የሚመጣ ስንቅም ተረፍረፍ ይልልናል፡፡

ከምሳ በኋላ ንግሥቲቱ የሚያስመጡት ድሮ ዳቦ ይቀርባል፡፡ ታራሚ በሙሉ የክት ልብሱን እንደየ ባህሉና ሀይማኖቱ ለባብሶና ተጋጊጦ ዝግጅቱን ማየት በሚችልበት በተዘጋጀው ቦታ ይታደማል፡፡ ይጀመራል፡፡ በፌሽታና በደስታ እስከ ቀኑ አስር ሰዓት ይከናወናል፡፡ ከአስራ አንድ ሰዓቱ ቆጠራ በፊት እቃው ይነሳሳና-እቃቃ ጨዋታው ተጠናቆ ተቆጥረን ይቆለፍብናል፡፡

የከርቸሌ ሴቶች ኪነት ቡድን በሀበሻ ቀሚስ ተውበው አበባዬ ሆይን እንዲህ እያሉ ያዜማሉ፡፡

«አበባዬ ሆይ - ለምለም(2)
ባልንጀሮቼ - ስሙኝ በተራ

እንጨት ሰብሬ - ቤት እንድሠራ
እንኳን ቤትና - የለኝም አጥር
ከርቸሌ አድራለሁ - ፍርዴን ስቆጥር!
እንኳን ወሩና ዓመቱ አለቀ
የለበስኩትም ተቦጫጨቀ::
ዘመዶቼም ሰለቹ
ፖሊሶችም ሰለቹ
እስካለን አላህ ያርግልን ምቹ!
ከብረው ይቆዩን - ከብረው!
ከዚህ እስር ቤት - ወጥተው!
ቤትና ትዳር - ይዘው!
መንታ - መንታ ልጅ ወልደው! ብለው ይመርቃሉ::

ከርቸሌ፣ በበዓል ቀናት በብሔር ብሔረሰቦች ዘፈን፣ በየዓይነቱ ይጨፈራል:: ከበሮ መጎሰም ይፈቀድልናል:: አዋቂ፣ ወጣት አይለይም ሁሉም ይጨፍራል፣ ይዝናናል::

የሙስሊሞች በዓል ሲሆን ደግሞ ለየት የሚለው ነገር ከክልል ውጭ ወጥተው፣ መስጊድ እንዲሰግዱ መፈቀዱ ነው:: በፖሊስ ታጅበው ሰግደው ሲመለሱ ከወንዶች ሙስሊም ታራሚዎች የሚበረከቱላቸውን የከረሜላ፣ ቸኮላት፣ ቴምር ስጦታ ይዘው ይመጣሉ::

በተለይ የረመዳን ፆም ወቅት፣ ታራሚ ሙስሊሞች ወሩን ሙሉ በዓንድ ሆነው፣ በህብር ሲሰግዱ ሲታዩ ለዓይን እጅግ ያስደስታሉ::

የሚያፈጥሩት ከቁጠራ ሰዓት በኋላ ስለሆነ ቡናቸውንና ሻያቸውን አፍልተው በፔርሙዝ ያስቀምጣሉ:: ጥብሳ ጥብሶቻቸውን በጊዜ ሲጠባብሱ ይውላሉ:: ፆሞችን በጋራ መፆም የተለመደ ነው:: የሙስሊሙን ክርስቲያኑ፣ የክርስቲያኑን ሙስሊሙ አብረው የሚፆሙ ብዙ ናቸው:: አሰፈጣሪውም ያንኑ ያህል::

ፆም ሲፈታ - «ዘካ» ይሰጣል::

ከንግሥቲቱ ጀምሮ፣ ከወንዶች ክልል፣ ከመስጊድ የመጣውን «ዘካ» ሁሉም በፆም ያሳለፉ ሰዎች እኩል መካፈል የተለመደ ነው::

ሌላው፣ እጅግ ደማቅ የከርቸሌ በዓል «ኢድ!» ነው::

የሙስሊሙን በዓል ደማቅ የሚያደርገው ሌላ ልዩ ነገር፣ የሚቀርበው

የከረሜላ፣ የብስኩት፣ የጥብሳ ጥብስ ብዛትና፣ የሚለብሱትና የሚያጌጡበት የጨሌ፣ የድርያና ጎጎራ ዓይነት፣ በሂና የተጌጠው ቆዳቸው ጭምር ነው::

* * *

ከርቸሌ፣ ለነፍሰጡሮችና ለእመጫቶች ለየት ያለ እንክብካቤና አያያዝ ይደረግላቸዋል:: ወፍራም ስፖንጅ ፍራሽ ከነአልጋው፣ አንሶላና ብርድ ልብስ፣ ፖፖ፣ አርቴፊሻል ከሰል፣ ዱቄት፣ ስኳር፣ ለሕፃናቱ የወር ደመወዝ ስልሳ ብር ይሰጣል::

እመጫቶች ከተፈቀደላቸው ክልል ውጭ ወደ ሌላ ታራሚ መቀላቀል አይፈቀድላቸውም:: ቁርስ፣ ምሳ፣ ዕራት እዛው በየክፍላቸው ይታደላቸዋል:: ተረኛ ባለ ኮታ ሆነው፣ ኮታ ለመውሰድ ካልሆነ በስተቀር ከክልላቸው አይወጡም::

እኛም ወደነሱ መድረስ አይፈቀድልንም:: ከነሱ ጋር የምንገናኘው በዓመታዊውና በየስድስት ወሩ በሚካሄደው አጠቃላይ የታራሚዎች ስብሰባ ላይ ነው::

በዚህ ሁሉ እንክብካቤ ተይዛ የነበረች አንድ ታራሚ መረበሽ - ጀምሯታል:: ማረሚያ ቤት አስር ዓመት ተፈርዶባት ስትገባ ልጇ ገና ዓመት'ንኳ አልሞላውም:: የልጇ አራተኛ ዓመት የልደት በዓል ሲከበር እኔም ታድሜ ነበር::

ልጇ አምስት ዓመት ሲሞላው ማረሚያ ቤት የመቆየት ዕድሉ ያከትማል:: ምክንያቱም «ክፉና ደጉን መለየት ሲጀምር እዛው ቢቆይ ለቀጣይ ሕይወቱ ስለሚያሰጋ ተብሎ ነው» አሉ::

አምስት ዓመት ሲሞላው፣ ይይዝልኛል ለምትለው ቤተሰብ ማስረከብ አለባት:: ግዴታዋ ነው! ልጇን ለማን እንደምትሰጥ ግራ የገባት ታራሚ፣ ፀባይዋ መቀያየር ጀምሯል:: አልፋ - ተርፋ ለብቻዋ ማውራት ጀምሯታል::

«የልጇን አባት በመድሀኒት ለመግደል ሞክራ» በዚህ ወንጀልዋ፣ ተፈርዶባት ነው የገባችው:: ብቻ ልጇን ለማንና እንዴት እንደሰጠችው አይታወቅም፣ እሷም ከመጫት ክፍል - ወደ ክፍል አራት ልጁ በገቢው የለም::

* * *

ሌላዋ ነፍሰጡር ታራሚ «እናቷን ለውርስ ብላ፣ በተኙበት አፍና መግደሏን ጎረቤቶች መስክረውባት» በቀጠሮ ወደከርቸሌ ወርዳ ነው። ገና የገባች ዕለት «ስንት ተፈረደብሽ» ሲሏት አዲስ አለመሆኗና፣ ታሪኳ የሚታወቅ መሆኑ ገባኝ።

ጠየም ብላ ግማሽ ፊቷን እስከ አንገቷ ድረስ ያበላሻት ጠባሳ፣ ከማስፈራቱም በላይ ክፉ ገፅታን አላብሷታል።

«እንኳን እናቷን፣ ወልዳ ልጇንም ከመግደል አትመለስም» እያሉ ያሚታል። ያብጠለጥሏታል። በሥራዋ በጣም የተፀፀተች ትመስላለች። ብቸኛና ገለልተኛ ነች። ሁሉም ሰው ስለርሷ እሚያወራ እየመሰላት ትጨነቃለች። ሁሉንም ሰው በዓይነ ቁራኛ የምትከታተለው ከዚህ በመነጨ ነው። ከሁሉም እመጫት ታራሚ ጋር ፀበኛ ነች።

አልፎ አልፎ የእናቷ ወዳጆች እየመጡ ይጠይቋታል። ያረገዘችለት ጓደኛዋ፣ በእናቷ ሞት ተጠርጥራ ከተያዘች ቀን አንስቶ ድራሹ ጠፍቶዋል። እሷም ስለሱ አንዲት ቃል ትንፍሽ አትልም። እናቷን የገደለችው እሱን ጠቅልላ አግብታ ለመኖር እንደነበር ያወራችው ላንዲት መቁርሷ ብቻ ነበር። ግን የከርቸሌ ወሬ አንዴ ከአፍ ከወጣ ሁሉም ሰማው ነውና፣ ሁሉም ሰው ይህን ጉዳይ ያውቃል።

እኔ በነበርኩበት ወቅት የነፍሰጡሮችና የእመጫቶች ቁጥር ሀያ ደርሶ ነበር።

«አሁንማ ከአዲስአቤዎቹ አልፈው ገጠሬዎቹም ልጆቻቸውን እያዘሉ ወንጀል ፈፅመው መምጣቱን ተያይዘውታል፣ እዚህ ያለውን አያያዝ ያስጠናቸው ሰው ያለ አይመስላችሁም?» እያሉ ታራሚዎች ያሽሟጥጣሉ።

ላቦሮዎችና ተመላሉዎች «እኔም ነገ ባረግዝ፣ ምን አጨናነቀኝ - ቀለል ያለች ወንጀል ሠርቼ እዚህ ገብቼ እታረሳለሁ» እያሉ ይመኛሉ።

* * *

በከርቸሌው የሽምግልና ኮሚቴ ውስጥ የሚያገለግሉና የመንደር ፅንስ አጨናጋፊ ሆነው ከሰላሳ ዓመታት በላይ «የህብረተሰቡን፣ በተለይ የሴቶችን

ቀንደኛ ችግር ስፈታ ነው የኖርኩት!» የሚል ስሜት የሚታይባቸው፣ በስልሳዎቹ አጋማሽ የዕድሜ ክልል የሚገኙት አዛውንት ታራሚ፣ በተለይ ለነፍሰጡርዋ ታራሚ የምክር አገልግሎት መስጠት ያዘወትራሉ:: ኮሚቴ ስለሆኑ እንደልብ እመጫት ክልል ወጣ፣ ገባም ይላሉ::

«በቀን - በቀን ከአምስት የያላነሱ ሴቶች በሬን ያንኳኩ ነበር!» የሚል ስሜት የሚታይባቸው እኚህ ታራሚ፣ ለሰባት ጊዜ እሳቸው ጋር ተመሳልሳ ያስወረደች ሴት እንዳለች ይናገራሉ::

«በነፍስ ማጥፋት» ቢከሰሱም፣ እሳቸው ግን የጎረቤት ጠላት ተነስቶባቸው ለእስር እንደበቁ ከዚህ በፊት ቀበሌዎች እጅ ከፍንጅ ይዘዋቸው በምክር እንደተለቀቁ እያሰቡ ተስፋ ያደርጋሉ::

አሮጊቷ፣ እዛው ከርቸሌ እንዳሉ ክስ በክስ ተደራርቦባቸዋል:: እሳቸው ፍርድ ቤት የማይቀርቡበት ወር ያለው ፍርድ ቤቱ በክረምት ሲዘጋ ብቻ ነው:: ተደራራቢና ተመሳሳይ አስራ አንድ ክስ አለባቸው:: ገና በመታየት ላይ ያሉት እንዳሉ ሆነው በተዘጉት ፋይሎቻቸው በድምሩ ዘጠኝ ዓመት ተፈርዶባቸዋል::

በተመሳሳይ ፅንስ በማጨናገፍ (በአፖርሽን) የገባች ሌላዋ ታራሚ ደግሞ እድሜዋ ወደ አርባዎቹ መጀመሪያ የሚገመት ሲሆን የሁለት ልጆች እናት ነች::

ቤተሰቧን የምታስተዳድረው ከዚህ ሥራ በምታገኘው ገንዘብ እንደነበርና ጥሩ ገንዘብ ስለምታገኝ ጥሩ ኑሮ ትኖር እንደነበር ታወራለች:: ባሏ እሷ ከርቸሌ ስትጋዝ ልጆቻቸውን ለእናቷ (ለአያታቸው) ጥሎ መጥፋቱን ስምታ ተደናግጣለች::

በግቢው ውስጥ ለደቂቃንኳ እረፍት የላትም ጥልፉንም፣ ሴንጀሩንም፣ ፈትሉንም፣ ፀጉር ሥራውንም አከታትላ እየተማረችና እየሠራች ገንዘብ አጠራቅማ ለልጆቿ ትልካለች::

ይህች ምንም ፋታ የሌላት ታራሚ ከቀን - ቀን ሰውነቷ እየከሳ፣ እየመነመነች ሄደች:: ማታ - ማታ በክፍሏ ካሉ ታራሚዎች ጋር አትነጋገርም:: ተኝታ ገንዘብ ስለሚያስገኝ ሥራ ስታወጣና ስታወርድ፣ ስታሰላስል ነው የምታመሽው:: እንቅልፍ አጥታለች::

ሀሳቡና በሽታው ተደራርበው አደቀቁዋት:: ለልጆችዋ የምትልከው ስታጣ ሁለተኛ ማንም ሰው መጥቶ እንዳይጠይቃት አደረገች:: ጠያቂዎቿም

ወር ሁለት ወር እያሉ ጠፉ!

ትምህርቱንም፣ ሥራውንም አልቻለችውም ተወችው:: «ነፍስ አልጠፋብኝም፤ ታመውብኝ ነው የከሰሱኝ፤ ብዙ ዓመታት የሚያስፈርድብኝ ይመስላችኋል?» እያለች ምክር መጠየቅ ጀምራለች:: በሁለት ችሎቶች የሚታዩ ተመሳሳይ ክሶች ስላሉባት ፍርድ ቤት ትመላለሳለች::

መቸም ከርቸሌ ያሉ ታራሚዎች ሕግ የተማሩነው የሚመስሉት:: ስለእያንዳንዱ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ምን እንደሚወስን ይተነብያሉ:: አብዛኛው ትንበያቸው ደግሞ ይሠራል:: ይሠምራል!

«አንቺ ግፋ ቢል በአንዱ ክስ ሁለት ዓመት፤ በሌላው ሁለት ወይም ሦስት ቢፈረድብሽ ነው፤ ትወጫለሽ እያሉ ያፅናኗታል::

«እስካሁን ሳይፈረድብኝ የታሰርኩትስ ከቁጥር ይገባል?» ትጠይቃለች::

እየተቀባበሉ ተመሳሳይ ግምት ይሰጣሉ:: እሷም ካለ ፍርድ ሁለት ዓመት የታሠረችውን እያሰላች:- «በቃ! ቢቀረኝ ሦስት ዓመት ብቻ ነዋ!» ብላ ተስፋ ታደርጋለች:: ትፅናናለች:: የፍርድ ቤት ቀጠሮዋ ሲደርስ ለልጆችዋ መልዕክት ታስተላልፋለች:: ፍርድ ቤት ይመጡላትና ታያቸዋለች::

ትልቁ ልጅዋ ሰባት ዓመት ቢሞላውም ትምህርት ቤት አልገባም:: ፍርድ ቤት አግኝታው እንደማይማር የነገራት ዕለት እያነባች ነው የመጣችው:: እናት መሆን መከራ! አቤት ስለልጆቿ እንዴት ትጨነቃለች::

ይህች ታራሚ ገና ፀሐይ ሳትጠልቅ ተቆጥረን ሲቆለፍብን «አይ! ስንት ጉዳይና ሥራ እያለን ጨለማ'ንኳ እንዲህ ይናፍቀን!?» እያለች ማማረር ልማዷ ነው:: ሊያበሽቋትና ነገር ሊፈልጓት ሲሉ «ጨለማ ናፈቀኝ! ጨለማ ብርቁ!» ይሏታል::

ከማረሚያ ቤቱ የሚሰጠንን የባቄላ ክክ ሽሮ ወጥ ከንግሥቲቱ በምንቸረችረው ሽንኩርትና ዘይት ከሽነን እንሥራና «እንብላ» ስንላት:-

«ልጆቼና እናቴ የሚበሉት አጥተው፣ በባዶ ቤት በረሀብ፣ በስቃይ እየተገረፉ፤ እኔ እዚህ ልንቀባረር አልችልም!» ብላ እምቢኝ ትላለች:: ትንሹን ልጇን ይዛ ባለመግባቷ ሁሌ ትፀፀታለች::

«እንዲህ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ትንሹን ልጄን ይዤ ገብቼ፤ ትልቁንም እያስተማርኩ፣ እናቴን እያገዝኩ የት እደርስ ነበር!» የሚል ቁጭት ውስጥ ውስጧን ይቦረቡራታል::

የክርስቲያኑንም፤ የሙስሊሙንም ፆምና ስግደቶች በእኩል በማከናወን

በመታወቋ «ያምና ፀሎቷን ክቡር ፍርድ ቤቱ ይቁጠርላት!» እያሉ ይተርቧታል፡፡

＊ ＊ ＊

በከርቸሌ ግቢ ውስጥ ከልጅነት እስከ እውቀት «በማደጎ» ልጅነት የምትታውቀው ላቦር (ሌባ) ጊደኛዬና፣ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠሩ እስረኞች «የንጉሣውያን ቤተሰብ» እስረኞች የነበሩበትን ዘመን አውርተው አይጠግቡም፡፡

ያውበትና የቁንጅናቸው ነገር ተገልፆ አያልቅም፡፡ እጅግ ሀዘንተኞችና፣ ሀይማኖተኞች፣ ሥርዓት አጥባቂዎች እንደሆኑ ይነገራል፡፡

የንጉሣውያን ቤተሰቦች ከርቸሌ በነበሩ ዘመን፣ ከርቸሌ እጅግ አስደሳች ቦታ ነበር አሉ፡፡ በርካታ ጠያቂዎች በቀን በቀን ይጎበኞዋቸው ነበር፡፡ በቀን እንዴ የሚፈልጉት ነገር ሁሉ ይገባላቸው ነበረ፡፡ የሚመጣላቸው ሳህን ተቆጥሮ አያልቅም፡፡

የነሱን ሳህን አስከፍታ በመቅመስ የወደለችዋን ፖሊስ «ከሁሉም ሳህን ስትቀምስ በቃ ምሳዋን ቻለች፡፡ ያውም ምርጥ ምሳ!» ይላሉ፡፡ ሰዓቷን በነሱ ጠያቂ ሰዓት ማመቻቸትዋን እያስታወሱ ይስቃሉ፡፡

በቀን በቀን ከሀምሳ ያላነሱ ሳህኖች እንደሞሉ እፊታቸው ይደረደራል፡፡ በነሱ የአመጋገብ ልምድ አብሮ በአንድ ትሪ መመገብ ጨርሶ አይታወቅም፡፡

የመመገቢያ የየግል ሳህኖቻቸውን ካቀራረቡ በኋላ፣ እጅ አስታጣቢ እጃቸውን ታስታጥብና ተከፍቶ ከተደረደሩት ሳህኖች በዓይነት በዓይነቱ ትንሽ -ትንሽ ከቆነጠሩ በኋላ ረዥም ሰዓት ወስደው ይመገባሉ፡፡ የሚበሉት ትንሽ ቢሆንም ለምን ያን ያህል ጊዜ እንደሚፈጁ የሚያስታውሷቸው ሁሉ የሚገረሙበት አንድ ትውስታ ነው፡፡

ከተደረደሩት የብፌ ምግቦች ሳይነኩ የሚቀሩ ሁሉ አሉ፡፡ ግን እነሱ በልተው እስኪጨርሱ መታገስ ግድ ነው፡፡ «ብዙዎቻችን ጎምዥተን ከወጣልን በኋላ ስለሚሰጡን ነው መሰል ሲሰጡን ሳናጣጥም ዋጥ - ዋጥ ማድረግ ይቀናናል» ትላለች ላቦሮዋ፡፡

«ምግባቸውን ልክ እንደነሱ እየቆነጠሩ ሳህን - ሳህናችን ላይ ሲጨልፉልን፣ አነስን ብለን እንቀውጣለን፡፡ ትንሽ ይሉንታ የያዘው ሰውም ቢሆን ይቁለጨለጫል፡፡

እነሱ ግን በማይሰማውና እጅግ ዝግ ባለ ድምፅ፣ ቅላፄ በተቀላቀለው

የዘወትር ንግግራቸው በተለይም ወጣቶችን፡-

«በናንተ ዕድሜ ብዙ ምግብ መመገብ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ቅርፃችሁ ይበላሻል፡፡ ገና በልጅነት ውፍረት ይመጣና በሽተኛ ትሆናላችሁ» በማለት ምክር መለገስ ይወዳሉ፡፡ «ምነው? ተስፋ ቆርጠሻል'ንዴ?» ይላሉ፡፡

«አንድ ቀን እንረብሻቸው ተባባልንና የሚተርፋቸውን ምግብ ለኛ ከመስጠት እንደማይድን አውቀን፤ ለናንተ የሚመጣላችሁን ምግብና የምታበሉን ነገር ምን እንደሆነ ስለማናውቀው፣ ከዛሬ ጀምሮ ዝርዝሩ (በሚኖ)፣ ከምን ከምን_እንደተሠራ ተጠቅሶ ይነገረን ብለን ጥያቄ እናንሳ» ተባብለን ተመካከርንና እንዴት እንደሚደናገጡ ገብቶን ማርናቸው» አለች አንድ አስታዋሽ፡፡

ሌላዋ በነሱ ዘመን የዓመት በዓል ጊዜ እንዴት ደማቅ እንደነበረ አስታውሳ ቀጠለች፡፡

«በተለይም ለእንቁጣጣሽ፤ እንደ ሕፃናቶቹ ወንዶች አበባ ስለን እንስጣቸዋለን፡፡ እንደገና «አበባዬ ሆይ» ዘፍነን ብዙ ብር እንቀበላቸዋለን፡፡ ሆያ-ሆዬ ሳይቀር እንጨፍርላቸዋለን፡፡ በሰበብ ባስባቡ እነሱን መቀባበል ነበር ሥራችን፡፡»

አንድ ቀን አንዲቷ ልዕልት፣ በዛ በታገተና ቅላፄ በሞላበት ንግግራቸው «መቸም በሀገራችን ሆያ-ሆዬ የሚጨፍሩት ወንዶች ብቻ ናቸው፡፡ እናንተ ሴቶቹ ታዲያ ምን ማድረጋችሁ ነው? ለማንኛውም ማታ መጥታችሁ ከኛ ጋር አምሹ፡፡» ብለው ፈቀዱ!

እደዚህ ዓይነት የጥሪ ምሽቶች የተለመዱ ነበሩ፡፡ ለየት ያለ ዝግጅት ሲኖራቸው እንደዚህ ነው የሚጠሩን፡፡ በጥሪ ቀን ቁጥ፣ ቁጥ ብሎ ነገር የለም፡፡ እምብርታችን እስኪገለበጥ መብላት ነው፡፡ በልተን፣ ጠጥተን፣ ጨፍረን፣ አመስግነንና መርቀን፣ የዓመት በዓል ስጦታዎች ተሰጥተውን እንሸኛለን፡፡»

ብቻ የነሱ ዘመን ከርቸሌ ይሞካሻል፡፡

* * *

በማረሚያ ቤቱ ታራሚዎች ሌላው በከፍተኛ ደረጃ የሚወራውና፣ ሁሌ በተስፋ የሚጠበቅ ጉዳይ ደግሞ የባለስልጣናትና የዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል

ድርጅት የሚያደርጉት ድንገተኛ ጉብኝት ዋናው ሲሆን፣ እንደ «የአገር ሉአላዊነት መደፈር» እና «ድልም» ለማረሚያ ቤት ታራሚዎች ትልቅ የመኖር ተስፋን የሚያጭሩ ታላቅ ታሪካዊ ክስተቶች በመሆናቸው በጉጉት ይናፈቃሉ።

ዳኞች፣ ባለሥልጣኖችና ቀይ መስቀሎች በፖሊስ አጃቢነት «ጉብኝት» ሊያደርጉ መሆኑ ሲሰማ ገና የሁሉም እስረኛ ሀሳብ «ምህረት ይኖር ይሆናል» ወደሚል አቅጣጫ ይዞራል። በተለይ ጉብኝቱ ዓመት በዓል መቃረቢያ ላይ ወይም በዓልን አስታኮ ከሆነማ «የምህረት» ተስፋ ግቢውን ያጥለቀልቀዋል።

«ምህረት የሚደረገው ለከባድ ወንጀለኞችና ከአስር ዓመት በላይ ለተፈረደባቸው ፍርደኞች ነው» ብለው የሚከራከሩ ይበዛሉ። ያምሆን፣ ይህ ጉብኝቱ የሚያመጣው ምህረት የለም። ፀጥ፣ፀጥ - በዛው ይረሳል።

የዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል ጉብኝት ወቅት ደግሞ ተሰባስበው በፖሊስ አጃቢነት በተለይ የፖለቲካ እስረኞችንና ጋዜጠኞችን ለብቻ እስከማናገር ይደርሳሉ።

ቶሎ፣ ቶሎ ባይመጡም፤ በመጡ ጊዜ የወር አበባ መቀበያ (ሞዴስ)፣ ሳሙና፣ ሶፍት፣ የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን በርከት አድርገው ስለሚሰጡን መምጣታቸው ይናፈቃል። ታራሚውን ብቻ ሳይሆን ቢሮውንም በልገሳ ስለሚያንበሸብሹት እነሱ ሲመጡ የግቢው መልክ ትንሽ ቀየር ያለ ሁኔታ ውስጥ ይገባል።

* * *

በማረሚያ ቤቱ የሴቶች እስረኞች ክልል ካሉ ጥሩ ነገሮች አንዱ ቤተ-መጽሐፍት (ላይብረሪው) ነው። ቤተ-መጽሐፍት ገብቶ ማንበብ ወይም መጽሐፍ ተውሶ (በኪራይ፤ በሳምንት 0.25 ሳንቲም አንድ መጽሐፍ ይከራያል) ማንበብ ይቻላል። ተማሪዎች የሆኑ ታራሚዎች እንደልብ መጽሐፍ ያገኛሉ። በተለይ እንግሊዘኛ መጽሐፍቶች ይበዛሉ። «በእርዳታ ስለሚገኙ ነው» ይባላል።

ጋዜጦች አዲስ ዘመንና አብዮታዊ ዲሞክራሲ እንደልብ ወቅት ጠብቀው ይመጣሉ። የግል ፕሬሶች ግን አንዳንድ ታራሚዎች በግል ከሚያስገቡዋቸው በስተቀር በላይብረሪው ውስጥ አይገኙም።

ከሰኞ - አርብ ባሉት የሥራ ቀናቶች በቤተሰብ አማካኝነት የየዕለት

ጋዜጣ የሚደርሳቸውና ሁሉንም ጋዜጦች የሚከታተሉ ንግሥቲቱ ብቻ ናቸው:: ደግነቱ ለራሳቸው አንብበው ሌላውም እንዲያነብ ስለሚፈቅዱ ተራዎን ጠብቀው ይደርስዎታል:: በዚህ መልኩ የየቀኑ ሁኔታ ይደርሰናል:: በየሳምንቱ ከአስር በላይ ጋዜጦችን ተዋውሰን እናነባለን::

ከላይብረሪው ውጭ ከቤተሰብም መጽሐፍ ከተላከ ይገባልናል:: ንግሥቲቱ በጣም ብዙ የእንግሊዝኛ መጽሐፍቶችን ሲያነቡ የሚውሉት ከውጭ እያስገቡ ነው:: አንዳንዴም ፊልሞችና ድራማዎች በቪዲዮ ካሴት ይመጡላቸዋል::

በነገራችን ላይ፣ በከርቸሌ ካሉ ክፍሎች፣ ከቁጥር አራት በስተቀር ሌሎቹ ጋር ቴሌቪዥኖች አሉ:: ቁጥር አራት ለምን እንደተዘለለ እንጃ! ታራሚዎች ግን ሌሎች ክፍሎች እየገቡ ያያሉ::

የንግሥቲቱ ቴሌቪዥን ከሁላችንም ይለያል:: ዴክ ጭምር አላቸው:: የማረሚያ ቤቱ ሳይሆን የግል ንብረታቸው ነው:: ማታ-ማታ ከቆጠራ ሰዓት በኋላ ከመረጡዋቸው አማሾች ጋር ድራማ ወይም ፊልም ሲያዩ ያመሻሉ::

በሌሎቹ ክፍሎች ባሉ ቴሌቪዥኖች ሁሌ ፀብና ንትርክ አይጠፋም:: የትግራይ ተወላጆች በነሱ ቋንቋ ሰዓት ይከፈት ብለው «ኡ - ኡ» ይላሉ:: ይከፈታል:: ኦሮምኛ ሲቀጥል ኦሮሞዎች «ኡ - ኡ» ብለው ይቀጥላል:: የአማርኛውን ፕሮግራም ማንም አይቃወምም::

ድምፅ መጨመርና መቀነስ አብዛኛውን ጊዜ ፀብ ስለሚያስነሳ እንዴ የተደረገው አይጨመርም - አይቀነስም::

በማረሚያ ቤቱ ያለን ታራሚዎች በዘር፣ በሀይማኖት፣ በእውቀት የተለያየን ሰዎች እንደመሆናችን መጠን፤ ታፍነን ስለምንኖር የሚያጣሉን ብዙ ጉዳዮች ይከሰታሉ:: በተለይ በቴሌቪዥን ወይም በጋዜጦች ጽሑፍ ላይ ተመሥርቶ የተነሳ ክርክር ቶሎ አይቋጭም::

በሌላ ጉዳይ የተጣሉትን ሁሉ ጠምዝዘው ወደ ብሔር ይወስዱትና በማታው የኢቲቪ ፕሮግራም ክፍለ ጊዜ ሰበብ አርገው የብሔር ፀብ ያደርጉታል:: ይህ ሁኔታ በተለይ በእመጫቶች ክፍል አዘውትሮ ይከሰታል:: ሁሌ ግምገማ ይደረጋል:: ለውጥ ግን አይመጣም::

ትችታቸውን ትግርኛ ፕሮግራም በቀረበ ዜና ወይም ዘፈን ወይንም ድራማ ላይ ይመሠርቱና ጉዳዩን አጠማዘው መበሻሸቅና ማሽሞር ይጀመራል::

ኦሮምኛ ሲቀጥል ደግሞ የትግሬዎቹ የራሳቸውን ሽሙጥና አሽሙር፤ የብሽሽቅ ሀሳብ ይሰነዝራሉ:: እነኝህ ሁኔታዎች የቀሰቀሱት ፀብ ቶሎ

አይበርድም። ቡድን፣ ቡድኖችን ይፈጥራል። አስተዳደር ድረስ ደርሶ ጨለማ ቤት እስከማስቀጣት የሚደርስ ወንጀል ከውስጡ ሊጎለጎል ይችላል።

* * *

በከርቸሌ ሕይወት የሚችሉትን ነገር ሠርቶ መሸጥ የተፈቀደና የተከበረ ነው። ያውም በሥልጠና ይደገፋል። በግቢው ያሉ የፖለቲካ እስረኞች የእጅ ሞያን የተካኑ ጥበበኞች ናቸው። የረቀቀ የጥልፍ አልጋ ልብስ፣ እርቦ፣ መሰበ ወርቅ፣ አገልግል በመሥራት ይሸጣሉ። ሥራቸው ጥራት ስላለው ጥሩ ዋጋ ያወጣላቸዋል። ማንኛውም ዓይነት በታራሚ ተሠርቶ ለሽያጭ የዋለ ዕቃ ቀረጥ ለማረሚያ ቤቱ ይከፈልበታል።

በግቢው ያሉ ፖሊሶች ከውሃ የቀጠነ ትዕዛዝ ሊያዝዎት ይችላሉ። ከፈለጉ ከቡና መውቀጥ እስከ ፀጉሬን ሥሪኝ ማስገደድ ማን እንደፈቀደላቸው አይታወቅም።

እነኝህ ባለሙያዎች «የአልጋ ልብስ ሥሪልኝ፣ ሹራብ ሥሪልኝ፣ መሶበ ወርቅ ጥለፊልኝ ...» እያሉ ያስገድዳሉ። «እምቢ» ማለት አይታሰብም። እንኳን እምቢ ማዘግየት የሚያመጣው ጣጣ ብዙ ነው። ፖሊሶችን በፀባይ መያዝ አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው። «አመክሮንና ዘመድ ጥየቃን ሊያሳግዱ ስለሚችሉ» ተብሎ ይፈራል።

ሌላው ፖሊሶች ጧት-ጧት፣ የቆጠራ ሰዓት ሲደርስ ከእንቅልፋቸው ደንብረው የመጡ እስኪመስለን ያን በፍርግርግ ብረት የተሠራን በርና መስኮት በዱላቸው ያለማቋረጥ እየነረቱ የሚያስጮሁት ለምን ይሆን? ምንም ያህል ዘመን ከርቸሌ ቢቆዩ የማይለመድ አስደንጋጭ መቀስቀስ!

ፖሊሶች ታራሚን ሲጠሩ «ማነሽ - አንቺ!» ማለት ይቀናቸዋል። ታራሚን የመጥላትና የመናቅ ባህሪ ይታይባቸዋል።

አቤት! በከርቸሌ ግቢ ቀን-ቀን ዝናብ አይምጣ! ያለው መሯሯጥና ጥድፊያ እጅግ አስገራሚ ነው። ፖሊሶች ተንደርድረው ይመጡና «ወደየክፍላችሁ!» ብለው እያደናበሩ አስገብተው ይቀልፉብናል። ዝናብ በከርቸሌ እጅግ የሚጠላ ነገር ነው። ጧት ሆነ፣ ምሳ ሰዓት ሆነ፣ በረንዳንኳ አይፈቀድልንም!

ህሉ ደግሞ በጣም ሩህሩህ፣ እናትና እህት የሆኑ ፖሊሶችም

አሉ፡፡ ስንታመም የሚጠይቁ፣ አጅቦ ወስዶ ለማሳከም በጣም መልካም ተባባሪ የሆኑ፣ ፍርድ ቤት አጅበው ሲወስዱ የሚያፅናኑ፣ ሻይ፣ ቡና፣ ሲጋራ የሚጋብዙ፡፡ የሚጋበዙም!

በየስድስት ወሩ ባለው የታራሚዎችና የፖሊሶች ግንኙነት ግምገማ ወቅት ስለ ፖሊሶች የፈለጉትን መናገር ቢፈቀድም፣ ማንም ደፍሮ አይሞክረውም፡፡ በተቻለ መጠን ከፖሊስ አለመጣላት ያዋጣል፡፡

* * *

ታሪኬን ስጀምር ባሏን ገድላ የታሠረችው የሦስት ልጆች እናት የሆነችው ወጣት ታራሚ (ከሁሉም ባለታሪኮች ለየት ስለሚልና፣ ዘርዘር አድርጎ ለመጻፍ ጭምር ይህን ያህል ዘግይቷል፡፡) የታሪኬ መደምደሚያ ነውና!

ይህች ታራሚ ፍርዷን የሰማች ጊዜ የሆነችውንና ያደረገችው ነገር እጅግ ዘግናኝ ነበር፡፡ በሷ ሀሳብ ለይግባኝ በላከችው ማመልከቻ መሠረት፣ ፍርድ ቤት ስትቀርብ እውነቱን ሁሉ ዝክዝክ አድርጋ ልትናገር፣ ከኛ ጋር ሁሉ ተመካክራ ጨርሳ፣ ፀጉሯን ሳይቀር ተሠራርታ የቀጠሮዋን ቀን ስትጠባበቅ፡-

የዕድሜ ልክ ፍርዷ ከተፈረደ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ማቅረብ የሚፈቀደውን የይግባኝ ማመልከቻ፣ ሰሚው አካል አይቶ ተከሳሹ በአካል በተገኘበት የመጨረሻ ፍርድና ፊርማ ይሰፍርበታል፡፡

ማንም ተከሳሽ የይግባኙን መጨረሻ በአካል ተገኝቶ እንደሚሰማ በአሠራር ተቀምጦ እያለ የዚች ታራሚ የይግባኝ ቀጠሮ ባልታወቀ ምክንያት ተዘለለ፡፡ በዕለቱ ፍርድ ቤት የሚቀርቡት ስም ዝርዝራቸው ተጠርቶ እንዲዘጋጁ ሲነገር የእርሷ ግን ስሟ ሳይጠራ ቀረ፡፡

በመጨረሻው የይግባኝ ቀን ልታፍረጠርጥ የነበረው፣ የአሰበችውና የተማከረችው ሁሉ ገደል ገባ፡፡ ባልታወቀ ምክንያት የይግባኝ ውሳኔዋ እዛው ከርቸሌ በፖሊሶች ተላከ፡፡ በጽሑፍ ነበር የተላከው፡፡

ትዕዛዙን ይዘው የመጡት ፖሊሶች በቀጥታ ለራሷ መስጠት ስላሰጋቸው፣ ከማረሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ጋር ተነጋገሩና በጥንቃቄ እንዲነገራት ተወሰነ፡፡ እሷ ግን ይህ ሁሉ አልገባትምና ፍርድ ቤት ለይግባኝ መቼ እንደተቀጠረች ለማወቅ መወትወቷን አብዝታለች፡፡

አንድ ቀን ቢሮ ተጠርታ እንድትረጋጋ ተመከረችና ውሳኔዋን እንድታነብ ተሰጣት፡፡ በፀጥታና በእርጋታ አንብባ ስትጨርስ ራሷን ስታ ተዘረረች፡፡ ፖሊሶች አፋፍሰው ሆስፒታል ወሰዱዋት፡፡ ሀኪሙ ከአጠገቧ ሰው እንዳይጠፋ አዘዘ፡፡

የግቢው ታራሚ በሙሉ በሷ ሁኔታ ተረበሸ፡፡ ግቢው ሀዘን አረበበበት፡፡ በየተራ ተመድበን እንጠብቃታለን፡፡ ለሦስት ቀናት ራሷን ሳታውቀ ከረመች፡፡ ንግሥቲቱን ጨምሮ መላው ታራሚ ተንከባከቡዋት፡፡

አገግማ፣ ከክሊኒክ ወደ ክፍሏ እንደተመለሰች ራሷን ለማጥፋት ኤሌክትሪክ ያዘች፡፡ በኃይል አፈረጣት'ንጂ አልገደላትም፡፡

በኃይል ከመውደቋ የተነሳ ጣውላው ቤት የተናደ እስኪመስል ጩኸት አሰማ፡፡ ፖሊሶችና ታራሚዎች ግር ብለን ስንገባ፣ ራሷን ስታ፣ ላብ-በላብ ሆና ተዘርራለች፡፡ አፋፍሰን ክሊኒክ አስተኛናት፡፡ በጣም ጎድቷታል፡፡ ሁለመናዋ ነጭ ሆነ፡፡ ብዙ ፈሳሽ እንድትጠጣ ታዘዘ፡፡ የፀጉር ቅቤ ሳይቀር እየቀባን፣ እያጠብን ተንከባክበን ያዝናት፡፡ ከአስራ አምስት ቀናቶች በኋላ ራሷን ማወቅ፣ መንቃት ጀመረች፡፡

በርግጥ እራስን በራስ ማጥፋት ትልቅ ወንጀል ሆኖ ቢያስከስስም፣ ከባድ ቅጣት እንደሚያስቀጣም ቢታወቅም፣ እሷ ግን በከባድ ማስጠንቀቂያ፣ በተግሳፅና በምክር ታለፈች፡፡

* * *

ይህች ታራሚ፣ ባሏን ገደለች ተብላ እድሜ ልክ ቢፈረድባትም፣ እርሷ ግን ጨርሶ ባሏን እንዳልገደለች ትናገራለች፡፡

«... ቡና ቤቴን ሸጬ፣ ከሱ ጋር ተጠቃለን በትዳር ስንኖር፣ የባለቤቴ የገንዘብ ምንጭ ምን እንደሆንኳን አላውቅም፡፡ ያለኝን፣ የነገረኝን አምኜ ነው የምኖረው፡፡

አባቴ ሞተዋል፡፡ ወላጅ እናቴ ግን በሞትና በሕይወት ባላ የተንጠለጠሉ ባልቴት ናቸው፡፡ ጥሩ ሕይወት እንደኖሩ ያስታውቃሉ፡፡ እጅግ ፀሎትና ፆም አጥባቂ፣ ሰውወዳድ አዛውንት ናቸው፡፡ ሦስት እህቶቹ ከሀገር ውጭ ናቸው፡፡

እናትየው በደርግ ዘመን ውትድርና ዘምቶ ድምፁ ስለጠፋው ልጃቸው ዘወትር ይጨነቃሉ፡፡

«የልጄን ዓይን አይቼ በማግሥቱ ልሙት!» እያሉ ይፀልያሉ፣ ይፆማሉ:: ይህ እኔ ያገባሁት ልጃቸው ግን ባልታወቀ ዘዴና መላ መላ ንብረታቸውን በሱ ስም እንዲሆን አስፈርሞዋቸዋል:: መኖሪያ ቤቱም፣ ድርጅቱም በሱው ስር ነው::

እህቶቹ እናታቸውን ተንከባክበ እንዲጦር፣ ተስማምተው አብረው እንዲኖሩ ተጨማሪ ርዳታም ያደርጋሉ:: ንብረቱን በሚመለከት የሚጠይቅ ማንም የለም:: እሱ ግን ማንንም አያምንም::

ባልታሰበና ባልታወቀ ወቅት ወንድሙ ከዘመቻ መጣሁ አለ:: የኮሌኔልነት ማዕረግ ነበረው:: ብዙ ዓመታት ግንባር ቢያሳልፍም፣ አሁን አዲስ ሕይወት የመኖር ህልም ያለው፣ ሰላማዊ ሰው ነው::

ሲመጣ፣ እጅና እግሩን ብቻ ይዞ ነው:: እናት ፀሎታቸው ስለሰመረ በሬ ጥለው ለሦስት ተከታታይ ቀናት «የቀም-ተዝካር» አወጡ::

ወዳጅ፣ ዘመድ፣ ጓደኛ፣ ጎረቤት ጠርተው የተጣሉትን ሁሉ ይቅር,ታ ጠይቀው፣ ርስ በርስ አገናኝተው አልጋ ያዙ:: ባሌ የወንድሙ መምጣት አላስደሰተውም:: ይህን ያስተዋሉት አዛውንት እናት ሽማግሌ ሰብስበው የንሰሀ አባታቸውን አስጠርተው ልጆቻቸው በተገኙበት ንብረት ሊናዘዙ በተያዘው ቀጠሮ፣ ይሄው የኔ ባል «ክፍለ ሀገር ሥራ አለብኝ» ብሎ ከቤት ጠፋ:: በዚህ ምክንያት እናት ያሰቡት ባይሳካም፣ የመሰላቸውን ለነፍስ አባታቸውና ለሽማግሌ በቃል ተናገሩ::

በሦስተኛው ቀን ባሌ ሲመጣ፣ እናቱ በጣም ደክመዋል:: ሆስፒታል እንዲተኙ ሲጠየቅ አሻፈረኝ አለ:: ሁለቱን ወንድማማቾች አስጠርተው እያለቀሱና እያቃሰቱ «ልጆቼ፣ እባካችሁ ተስማሙ!» አሉዋቸው::

እናት ደክመው እየተጠበቀ፣ ወንድማማቾቹ ሳሎን ቤት ትልቅ አተካራ ገጠሙ:: ኮሌኔል ሽማግሌ ተጠርቶ እናቱ የመጨረሻ ቃላቸው በጽሑፍ እንዲሰፍር ሲጠይቅ፣ ወንድምየው «እናቴ አሟታል - ደክሟታል ትተኛበት» ብሎ፣ ተበሳጨሁ አለና ልብሱን ቀያይሮ መኪናውን አስነስቶ ቤቱን ለቆ ወጣ:: አደረ::

ሌሊቱን እናታቸው አረፉ!

ወንድማማቾቹ የእናታቸውን ሥርዓተ ቀብር እስከ አርባው ቀን ተቻችለው አደረሱት:: «ኑዛዜ የሚሰማው የአርባው ቀን ከሐውልት ምርቃ ሥርዓት በኋላ ነው ተብሎ ቀጠሮ ስለተያዘ» ከመተታገስ ውጭ አማራጭ

ስላልነበረ ሁሉም ፀባይ አሳምረዋል::

የአርባው ድግስ በጣም ትልቅ ነበር:: መላው ዘመድ አዝማድ፣ ጎረቤት፣ ጓደኞች የወንድማማቾቹን መጨረሻ ለማየት ሲያንሾካሹኩና ግምት ሲደረድሩ ከርመዋል:: በጉጉት ይጠበቃል::

የአርባው ድግስ ሲጠናቀቅ፤ ሲረፋፍደና እንግዳው ተሸኝቶ ጋብ ሲል:: ነፍስ አባት ተብየው ወንድማማቾቹንና ቤተሰብ የሆኑ አንድ አራት ሰዎችን ጨምረው፤ መኝታ ቤት ስብሰባ ተቀመጡ:: ዝርዝሩ ብዙና የተለያየ ቢሆንም ብቻ «ሁሉንም ንብረት በኔ ባል ቁጥጥር ሥር ሆኖ ኮሌኔሉ እሱ እንዳለው እንዲተዳደር» የሚል ነው ማሳረጊያው::

ኮሌኔሉ ከዚህ ቀን በኋላ ጥርሱን መንከስ ጀመረ ምንም ዓይነት ጥያቄና መልስ አላነሳም:: ፀጥ አለ:: ከእናታቸው ሰማንያ በኋላ ኮሌኔል ጥቂት የወንድሙን ጓደኞች እኔን ሚስቱን ጨመረና ወንድሙ መቋቋሚያ ሰጥቶት፣ ቤቱን ለቆ የራሱን ሕይወት እንዲመራ እንዲያስችለው ለመነ:: አስለመነ::

ወንድምየው ቤት መከራያና ለይስሙላ ረዳሁ የሚያስብል ነገር አደረገና ሌላውን ጉዳይ አሻፈረኝ አለ:: «ኤምባሲ ተቀጥሮ መሥራትና መኖር ይችላል!» ይላል ስለወንድሙ ሲጠየቅ:: ይህ ሁሉ ሲሆን ኮሌኔሉ ለኔም ሆነ ለልጆቼ፤ ለሁሉም ሰው ጥሩና ቀና አሳቢ ነበር ለማለት ይቻላል:: በወንድሙ ከመናደድ ይልቅ ስለወንድሙ መጥፎነት እያሰላሰለ ይጨነቃል!

«አንድ ወንድሜ ነው፤ እናቴ ደግማ አትወልድልኝም:: ሕይወትን ስላላየ ስላላሳለፈ ነው፤ መስሎት ነው ...» እያለ ይቅርታ ለወንድሙ ማድረግ ይፈልጋል:: እኔን የሚሠራኝን ግፍ እያየ፤ እያመረረ፣ እየጨከነ መጣ::

ኮሌኔል ሁሌ አይዞሽ ባዩ ነው:: ልጆቼን እንድጠይቅ አልፎ አልፎም ቢሆን ጓደኛዬ ቤት እንድሄድ ይመክረኛል:: ያፅናናኛል:: በቀን አንዴ ቢያንስ ይደውልልኛል:: ባለቤቴ ባሻው ቀን፣ ባሻው ሰዓት ከፈለገ ሰው ሰብስቦ ጫት ተሸክሞ መጥቶ እንዳስተናግድ ያስገድደኛል:: በጓደኞቹ ፊት እጅግ ሊያባብለኝ ይሞክራል:: ቅመው ሲጨርሱ እንደ ሴት ለባብሶ መኪናውን አስነስቶ ሲወጣ መቶ ብር ይሰጠኛል:: የለት ደመወዜ መሆኑ ነው::

* * *

የወንድማማቾቹ ቅራኔ እየሰፋና እየተባባሰ በመጣ ቁጥር እኔ ተጨንቄ

ልሞት እደርሳለሁ:: ከኮሌኔሉ ጋር ስለባሌ፣ እሱ ስለወንድሙ ጭካኔና በደል እያወራን እኩል እንማረራለን::

ልጆቼን ልጠይቅ ስሄድ አብሮኝ ይሄዳል:: አንዳንዴ እኔ ሳልሰማ ሁሉ ሄዶ ያዝናናቸዋል:: ይጠይቃቸዋል:: ልጆቼ፣ የልጆቼ አሳዳጊዎች (አያቶቻቸው)፣ እኔም ለኮሎኔል ትልቅ ክብርና ፍቅር ነበረን::

ባለቤቴ ባዶ ቤት ጥሎኝ ከጠፋ ሰነባብቷል:: ልብስ በሻንጣ ይዞ ሲወጣ አምስት መቶ ብር ሲሰጠኝ ራቅ ያለ ቦታ እየሄደ መሆኑ ገባኝ:: በዚህ ጊዜ ጊደሮቹንና ጊደሮቹን አማከርኩና፣ ሽምግለውን፣ ንብረቴን አስጥተው እንዲያለያዩኝ በየቤታቸው አጠያይቄ እግራቸው ላይ ወደቅኩ:: ይህን እንዳደርግ በይበልጥ የመከረኝ ኮሎኔል ነው::

የት እንደሚውል፣ ምን እንደሚያደርግ፣ ከነማን ጋር እንደሚዝናና ኮሎኔል ጠንቅቆ ያውቃል:: ኮሎኔል በተፈጥሮው ዝርዝር ነገር መናገር አያበዛም::

«ምን ላርግ?» ብዬ ሳማክረው ነው ይህን አርጊ ያለኝ:: ጊደኛዬም ተስማምታለች:: በጋራ ነው:: ሽማግሌዎቼን ሰብስቤ ከጨረስኩ በኋላ ስለሚፈጠረው ነገር እያሰብኩ መጨነቅና መጠበብ ሆነ ሥራዬ:: ልጆቼን ሄዶ ማየት ሁሉ አስጠላኝ:: ምን ይገኛ? አቃተኝ::

ከሄደበት መጥቶ እስኪለይልን ኮሎኔልን'ንኳ ማግኘት አስጠላኝ:: በአስራ አምስት ቀኑ እኩለሌሊት ገደማ ስልክ ደወለና በር እንድከፍትለት አዘዘኝ::

አስራ አምስት ቀን ብቻዬን፣ ተዘረፈ፣ ሌባ-ገባ፣ ጊ-አለ እያልኩ ስጨነቅ እንቅልፌ ሁሉ ተረባብሾ፣ ምግብ አስጠልቶኝ እጣን እያጨስኩ ወተት በዳቦና ውሃ እየጠጣሁ ተጎሳቁዬ ነው የከረምኩት::

የመኪናውን ድምፅ እንደሰማሁ ተንደርድሬ በር ከፈትኩ:: መኪናውን አስተካክሉ አቆመና በር ዘግቼ ስጨርስ በጥፊ ተቀበለኝ:: እሮጬ ቤት ስገባ ተከተለኝና የዱላ መዐት ያወርድብኝ ጀመር:: በዛሬው ቀን፣ ባሁኗ ደቂቃ ቤቱን ጥዬ ካልሄድኩ ጉዴ እንደሚፈላ ሽጉጡን አውጥቶ እያሳየ አስጠነቀቀኝ::

በዛ ምሽት፣ በፒጃማ፣ በነጠላ ጫማ፣ ፀጉሬ እንደተንጨበረረ፣ ነፍሴ አውጭኝ ብዬ ወጥቼ መንገድ ገባሁ:: አስፋልት እስክደርስ የማውቀው ነገር አልነበረም:: መንገዱ ረጭ ብሎ ምንም ነገር አይንቀሳቀስበትም:: የልቤ ምት አፍኖ የሚገለኝ መስሎኝ ነበር::

አስፋልት ስደርስ የት ልሂድ ብል መሄጃ አጣሁ:: ጥግ - ጥጉን እያለቀስኩ

ጊደኛዬ ቤት ደረስኩ። በዛ ጠራራ ሌሊት፣ በዛ ላይ ስደርስ አላመንኩም ነበርና በሩን በኃይል ደብድቤ መላ ቤተሰቡ ከእንቅልፍ ነቁ። በር የከፈተልኝ የሚፈራው ታላቅ ወንድሟ በሙሉ እቅፍ ሲቀበለኝ የባሰ አለቀስኩ።

ሊያባብለኝ የደፈረ የለም። ሁሉም የሳሎኑን ሶፋ ከበው አላቀሱኝ። እናቷ እምነትና ፀበል ቀቡኝና ከሌሊቱ አስር ከሀያ ዱቄት ቡና ተፈልቶ፣ እራት በልቼ እንድተኛ አደረጉ።

ጠዋት እንድተጣጠብ፣ እንድረጋጋ መከሩኝ። ረፋዱ ላይ ባለቤቴ ሰተት ብሎ መጣና አንዴ ሳናግራት ብሎ «ሰሞኑን ጊዜ ሳገኝ አነጋግርሻለሁ፣ ያው ብሎ ሁለት መቶ ብር ሰጠኝና» እነሱን አክብሮና አመስግኖ ወጥቶ ጥርግ አለ።

ለኮሎኔል ስልክ ደውዬ የሆነውን ሁሉ ስነግረው ሊያየኝ መጣ። አባብጩ ሲያየኝ በጣም አዘነ። ጊደኛዬንና ሽማግሌዎቹን አሰባስቤ ለባሌ ላኩበት።

«እቤቷ ትግባ!» አለ።

ሽማግሌዎቹም ሰለቹ።

አንድ ሳምንት ጊደኛዬ ቤት ስቀመጥ፣ ስልክ እንኳ ደውሎልኝ አያውቅም። ምን ማድረግ እንዳለብኝ የሚመክረኝ ጠፋ። ኮሎኔል ፊትሽም ድኗል፣ ልጆችሽ ናፍቀዋል አብረን እንያቸው ብሎኝ አያታቸው ቤት ሄድን።

ኮሎኔል እኔን ለማፅናናትና ለመርዳት ብዙ ፍላጎት ቢኖረውም ጊደኛዬ ባልሽ ሰምቶ ይገልሻል ብላ ስላስፈራራችኝ ብዙ አብሬው አልታይም።

ልጆቼን ልጠይቅ ስሄድ ቤት አያታቸው መኝታ ቤት አስገብተው «እንደው ልጄ - ደህና ነሽ ወይ? እባክሽ የልጄ ምትክ ነሽ፣ ከከፋሽ እዚህ ነይና ከልጆችሽ ጋር ተቀመጪ!» ሲሉኝ፦

በጣም ተደናግጬ «እሺ ሳስብበት!» አልኩ።

ሲሰናበቱኝ፣ አንገቴ ስር እየሳሙኝ፦

«ልጄ እባክሽ ተጠንቀቂ! - ተጠንቀቂን!» ሲደጋግሚት፣ ምን ታይቷቸው ነው ብዬ ተረበሽኩ። ኮሎኔል አስር ጊዜ «ምን ሆንሽ?» ሲለኝንኳ መመለስ አቃተኝ። ጊደኛዬ ቤት ቶሎ እንዲመልሰኝ ተማፀንኩት። አላመነታም። አደረሰኝ።

ጊደኛዬ ፊልም ተከራይታልኝ፣ መልዕክት ትታ ሄዳለች። በቤቱ ውስጥ ማንም የለም። እኔ «ልጄ - ተጠንቀቂ!» የሚለው የአሮጊቷ ድምፅ እየተስተጋባብኝ ተረብሻለሁ።

«ልጄ - ሰሞኑን ቅዠት ሊገለኝ ነው፣ አንቺ ግን ደህና ነሽ?» ብለው ገና ሲያዩኝ ሲጠይቁኝ መረበሽ ጀምሮኝ ነበር:: ልጆቼም የተለየ አሳሳም የሳሙኝ እየመሰለኝ፣ አሁንም ሳስታውሰው እበጅ - እበጅ ይለኛል» አለች::

«ጊደኛዬ ፍርድ ቤት ከሰሼ ሀብቴን እንዳገኝ ብትመክረኝም፣ እንኳን ለፍርድ ቤት ለታክሲ'ንኳ የለኝም:: ኮሎኔልም ይህን ሁለት ቀን ጠፍቷል::

ቀኑ ቅዳሜ ነው:: ጊደኛዬና መላቤተሰቡ ሠርግ ተጠራርገው ሲሄዱ ብለመን አንገቴን በቢላ ብዬ ፊልም ተከራይተውልኝ ሄዱ:: ፊልሙን ለይስሙላ ከፍቼ ብዙ ያሳለፍኳቸውን ቅዳሜዎች እያሰላሰልኩ ስልኩ አቃጨለ::

ኮሎኔል ነበር የደወለው:: እየመጣ እንደሆነና ለባብሼ እንድጠብቀው፣ በጣም እንደሚፈልገኝ ትዕዛዝ መሰል መልዕክት ነው የነገረኝ:: ድምፁ ልክ አልነበረም::

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ ነው::

ደንግጬ ልጆቼ ጋር ደወልኩ:: እያታቸው «ደህና ነሽ?» መቼ ብቅ ትያለሽ?» ሲሉኝ ግራ ተጋባሁና «ሰሞኑን» ብዬ ቶሎ ዘጋሁና መለባበስ ጀመርኩ::

ኮሎኔል እኔ ጋር ለመድረስ ግማሽ ሰዓት አልፈጀበትም:: በትንሿ ኮንትራት ታክሲ ነው የመጣው:: በር ቀልፌ፣ ቁልፍ እስከማስቀምጥ'ንኳ ፋታ አልነበረውም::

«ምነው ደህና አይደለህም?» ስለው መልስ ሳይሰጠኝ አደናብሮ ታክሲ ውስጥ ጨመረኝና «ንዳው!» ብሎ አዘዘ:: ወዴት እንደምንሄድ አላውቅም:: ኮሎኔል ቁና-ቁና ይተነፍሳል:: በጣም ተጨነቅኩ::

ባለታክሲውን «ሙዚቃ፣ ሬድዮ የለህም?» ሲለው፣ በፍጥነት ከፈተለት:: ድምጹ ሞቅ አድርጎ አስጨመረ::

የት እንዳለን'ንኳ ማወቅ ተሳነኝ:: ባለታክሲው ተነግሮታልና እያቆራረጠ ይነካዋል:: ጥቅጥቅ ወዳለ ጨለማ ቦታ ስንደርስ ታክሲውን አስቆመና ሁለታችን ወረድን:: ወንዝ ያለበት ቦታ አፋፍ ላይ አቆመኝና ሽጉጡን ሲያወጣ ጊንት ማድረጉን አየሁ:: የሚናገረው ሁሉ የጠፋው ይመስላል::

ጥርሱን ሲያንቀራጭጭ ላብ አሰመጠኝ::

«ያንን አውሬ'ኮ - ገደልኩት!» አለኝ በቁጣ:: በርከት ያሉ ማስፈራሪያና ቁጣዎችን ሲያወራ እንደነበር ብቻ አስታውሳለሁ::

«አሁን አንቺን የፈለግሁሽ ለአንድ ነገረ ብቻ ነው:: ይህን ካልፈፀምሽ

አንቺም፣ ልጆችሽም ያልቅላችኋል!» ሲለኝ ሲአል የገባሁ ያህል ተርበተበትኩ።

«እኔን'ኳን የናቴን ልጅ፣ ወንድሜን ገድያለሁ። ከዚህ የበለጠ የሚያስፈራ ነገር የለም። አንቺ አሁን ሄደሽ ለፖሊስ ገደልኩ ብለሽ እጅሽን ትሰጫለሽ።» በማለት እንዴት እንደገደለው ነገረኝ።

የባሌን ጓደኛ ስም ጠርቶ «እሱ ቤት በፍራሽ ዙሪያ ተቀምጠው ጫት ሲቅሙ በቀዳዳ አይቼ፣ እጄን ብቻ አሾልኬ ግንባሩን አልኩት! ከጓደኞቹ መሀል ነጥዬ ደፋሁት!» አለኝ።

ባሌን ገደልኩ ብዬ ሦስተኛ ጣቢያ እጄን እንድሰጥ፣ ሽጉጡን ጆሮዬ ስር ደግኖ ለሚጠይቁኝ ጥያቄ ምን እንደምመልስ፣ እየጠየቀኝ - እየመለስኩ አለማመደኝ። ሦስተኛ ጣቢያ ድረስ ራሱ አደረሰኝ።

ስንደርስ፡-

«አይዞሽ፣ ሁሉንም ጉዳይ በገንዘብ አስጨርሼ በስድስት ወር ውስጥ አስፈታሻለሁ። ከዛ በላይ አትቆይም!» አለኝና ሽጉጡን ሰጥቶኝ በርቀት ያየኛል።

እየተንቀጠቀጥኩ፣ ሽጉጥ ይዤ ያዩኝ ፖሊሶች ሲጠይቁኝ «ባሌን ገድዬ!» ስላቸው እያንደረደሩ ለመርማሪው ወስደው አስረከቡኝ።

መርማሪው ዝርዝር ጥያቄ እየጠየቀ ይሞግተኝ ጀመር። ካርቦን፣ እስክሪብቶና ወረቀቱን አመቻችቶ ተዝናንቶ ሲያዋራኝ፣ እኔ ኮሎኔሉ «አንዲት ምስጢር ብታወጪ በልጆችሽና ባንቺው ሕይወት መፍረድሽን እወቂ!» ያለኝ ያስተጋባብኛል።

«እንኳን ላንቺ - ለእናቴ ልጅ ደንታ እንደሌለኝ ይግባሽ!» እያለ የጬኸብኝ አስተጋባብኝ።

ፖሊሱ ለጠየቀኝ ጥያቄዎች ኮሎኔል ያስጠናኝን መለስኩና፣ ገድያለሁ ብዬ የጻፈው መአት ወረቀት ላይ እያንዳንዱ ገጽ ላይ ፈርሜ ማረፊያ ቤት ገባሁ።

በሳምንቴ ፍርድ ቤት ቀረብኩ። ክሴ ተነበበልኝና ኮፒውም ተሰጠኝ። «ክሱን ትቃወሚያለሽ?» ስባል «አልቃወምም!» አልኩ።

ፖሊስ ጣቢያ እያለሁ ኮሎኔል ብርድ ልብስ፣ ገንዘብና ፍራሽ አስልኮልኛል። ሰባት ወራት ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ስቆይ የኮሎኔል እርዳታና ማፅናናት አልተለየኝም።

ከርቸሌ ስወርድ «አይዞሽ፣ ጠበቃ አቁሜልሽ ተከራክሮ ነፃ ሊያወጣሽ

ነው! ትንሽ ታገሺ!» የሚል መልዕክት ላከልኝ:: እስር ቤት ልጆቼን ይዞ መጥቶ አሳይቶኝ ሁሉ ያውቃል::

ከርቸሌ እንደገባሁ ኮሎኔል ጠፋ:: የልጆቼን አያት እንዲያፈላልጉልኝ ብማፀንም ፈልገው አጡት:: ንብረቱን ሁሉ ሻሽጦ፣ ገንዘቡን አሰባስቦ፣ እኔንም ዕድሜ ልክ እንዲፈረድብኝ አርጎ ነው የጠፋው::

የዕድሜ ልክ እስራት ሲፈረድባት ነው ዕውነቱን ለኛንኳን ያጫወተችን:: እናም በይግባኝ ሁሉን ነገር ልታፍረጠርጥ ወሰነች:: ግን አልሆነም!

የይግባኝ ውሳኔዋ እዛው ከርቸሌ፣ ባለቸበት እንድታውቀው መደረጉ ትክክል እንዳልነበረና ሕጉ-ወጥ ሥራ መሠራቱን ፖሊሶች ሳይቀሩ አውቀዋል:: በገንዘብ እንዲህ ሊሠራ እንደሚችልም ግምታቸውን የሰነዘሩ ነበሩ::

ይህችን ታራሚ አንድ ቀን ልጇ ሊጠይቃት መጥቶ «እማዬ! እውነት ሰው ገለሽ ነው የታሰርሽው?» ብሎ ከጠየቃት በኋላ፣ ማንም ሰው እንዳይጠይቃት አደረገች::

(ተፈፀመ)
1998ዓ.ም

ለመልዕክትዎ:- የመልዕክት ሳጥን ቁጥር
21728
ኮድ ቁጥር 1000
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ



በከርቸሌ ግዙፍ ዓለም ውስጥ በድንገት ከተሠራ ስህተት የተረፈ እልፍ ፀፀትና ንዴት፣ በበቀልና በጥላቻ በተፈጸመ የክህደት ሰንሰለት እንደየወንጀሉ ዓይነት፣ ሰዎች ማንም ተመልካች በሌለበት እስር ቤት ውስጥ ብዙ በደሎች ይደርሱባቸዋል፡፡ በግቢው ውስጥ ያለነው ታራሚዎች በእኩል ዓይን አንታይም! ፖሊሶች፣ ሲያላግጡ «እኩል የምትሆኑት ፍርድ ቤት ብቻ ነው!» ይላሉ፡፡

እውነትም ነው!

(ከመጽሐፉ የተቀነጨበ)

ዋጋ ብር 10.00

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ